## ሦስተኛው ፡ ከዲኑ ፡ የተሰጠ ፡ ዓመታዊ ፡ መግለጫ ።

## ስለ ፡ ፲፱፻፶፰ ፡ ዓ. ም. የትህምርት ፡ ዓመት ፡ የተሰጠ ፡ መግለጫ ።

ከጀምስ ፡ ሲ. ኤን. ፖል ።

ባለፈው ፡ ዓመት ፡ ከተፈጸሙት ፡ ተግባሮች ፡ ከፍተኛውን ፡ ቦታ ፡ የያዘ ፡ ድርጊት ፡ ሰኔ ፡ ፳፬ ፡ ቀን ፡ የተፈጸመው ፡ ድርጊት ፡ ነው ። ይህም ፡ ሦስተኛውና ፡ ቍጥራቸው ፡ ላቅ ፡ ያለ ፡ ተማሪዎች ፡ የተመረቁበትና ፡ የዩኒቨርሲቲውን ፡ የኤል ፡ ኤል ፡ ቢ ፡ (የሕግ) ፡ ዲግሪ ፡ ለማግኘት ፡ ብቁ ፡ የሆኑትን ፡ ይህንኑም ፡ ክብር ፡ ለመቀዳጀት ፡ የመጀመሪያዎቹ ፡ የሆኑትን ፡ ተመራቂዎች ፡ ለዩኒቨርሲቲው ፡ ቻንስለር ፡ ለግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ አቅርቤ ፡ ለማስመረቅ ፡ ዕድል ፡ ያገኘሁበት ፡ ቀን ፡ ነበር ። ይህም ፡ ለኔ ፡ ታላቅ ፡ ክብር ፡ ነው ። ቀጥሎም ፡ ሰኔ ፡ ፳፮ ፡ ቀን ፡ አስመራ ፡ ባለው ፡ ይህ ፡ ፋኩልቲ ፡ በሚያካሂደው ፡ የማታ ፡ ትምህርት ፡ ፕሮግራም ፡ ለሁለት ፡ ዓመት ፡ ሲከታተሉ ፡ ለቆዩት ፡ ተማሪዎች ፡ የሕግ ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ፡ በመስጠት ፡ የመጀመርያውን ፡ የምረቃ ፡ ቀን ፡ አከበርን ።

ባ፲፱፻፶፰ ፡ ዓ. ም. በተፈጸሙት ፡ ምረቃዎች ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤቱ ፡ (ፋኩልቲ) ፡ እመጀመሪያው ፡ ምዕራፉ ፡ ላይ ፡ ደርሶአል ። ምናልባትም ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤቱን ፡ (ፋኩልቲ) ፡ የመጀመሪያ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ታሪክ ፡ ባጭሩ ፡ ማውሳት ፡ ተገቢ ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ።

## የመጀመሪያዎቹ ፡ ሁለት ፡ ዓመታት ።

የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ አቋሙ ፡ ከምላ ፡ ጐደል ፡ ሆኖ ፡ ባ፲፱፻፶፭ ፡ ዓ. ም. ተቋቋመ ። እንዲህ ፡ ዓይነቱ ፡ ድርጅት ፡ ሲጀመር ፡ የሚያጋጥሙትን ፡ የተለመዱ ፡ ችግሮች ፡ ተቋቋምናቸው ፤ ከነሱም ፡ ውስጥ ፡ የትምህርቱን ፡ ፕሮግራም ፡ ፕላን ፡ ማውጣት ፡ ባጭር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ የፋኩልቲውን ፡ ባልደረባዎች ፡ መቅጠር ፡ ሥራው ፡ የተሟላ ፡ ለማድረግ ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ ማዘጋጀት ፡ ድርጅቱን ፡ ለማቋቋም ፡ የሚያስፈልጉትን ፡ ተጨማሪ ፡ የሆኑ ፡ ከባድ ፡ ወጪዎች ፡ ለመክፈል ፡ ይረዱን ፡ ዘንድ ፡ የውጭ ፡ እርዳታዎችን ፡ ማግኘት ፡ ነበሩ ። ይህ ፡ ሁሉ ፡ በተቻለ ፡ መጠን ፡ የሕግን ፡ ሥራ ፡ ከፍ ፡ ወዳለ ፡ ደረጃ ፡ በሚያደርስና ፡ በሕግ ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ የተሰማሩትን ፡ ሁሉ ፡ ለማስተባበር ፡ በሚረዳ ፡ ዘዴ ፡ በተቻለ ፡ ፍጥነት ፡ እንዲፈጸም ፡ አስፈልጐ ፡ ነበር ። ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ የታተሙ ፡ ማስተማርያ ፡ የሚሆኑ ፡ መጻሕፍት ፡ ስላልነበሩ ፡ ለወደፊቱ ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ጠቃሚ ፡ መጻሕፍት ፡ ይሆናሉ ፡ ብለን ፡ ተስፋ ፡ በማድረግ ፡ ለየትምህርቱ ፡ መማሪያ ፡ የሚሆኑ ፡ ጽሑፎች ፡ እኛው ፡ ራሳችን ፡ እያዘጋጀን ፡ መስጠት ፡ ግድ ፡ ሆነብን ። በሰባት ፡ መምህራን ፡ በ፳፫ ፡ የቀን ፡ ተማሪዎችና ፡ ባ፵ ፡ የማታ ፡ ተማሪዎች ፡ ትምህርት ፡ ተጀመረ ።

ከመጀመሪያው ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ መሠረታዊ ፡ የሆኑ ፡ ብዙ ፡ ውሳኔዎች ፡ ተወሰኑ ። ከነዚህም ፡ አንዱ ፡ አሁን ፡ ከሕግ ፡ ሥራ ፡ ክንውን ፡ (አድሚኒስትራስዮን) ፡ ጋር ፡ ግንኙነት ፡ ላላቸው ፡ ሰዎች ፡ ከዲግሪ ፡ ደረጃ ፡ በታች ፡ የሆነ ፡ መሠረታዊ ፡

የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ለመስጠት ፡ የማታ ፡ ትምህርትን ፡ ማደርጀትና ፡ ማስፋፋት ፡ ነበር ። ይኸም ፡ የማታ ፡ ዲፕሎማ ፡ ፕሮግራምን ፡ በመክፈትና ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ፡ ፕሮግራምን ፡ በማስፋፋት ፡ ተከናወነ ። ሁለተኛው ፡ ውሳኔ ፡ እዚህ ፡ በሕግ ፡ ትምህርት ፡ (ቢያንስ ፡ ትምህርት ፡ ቤቱ ፡ ገና ፡ በመደርጀት ፡ ላይ ፡ ባለበት ፡ ዘመናት) ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ፡ ብለን ፡ የምንቆጥረውን ፡ ሁኔታ ፡ ለመጠበቅ ፡ የትምህርት፡ ቤቱን ፡ ባልደረቦች ፡ ብዛት ፡ መጨመር ፡ ነበር ። ይኸውም ፡ አስፈላጊ ፡ የሆነበት ፡ ምክንያት ፡ ለትምህርት ፡ የሚሆኑ ፡ መጻሕፍትና ፡ የሕጉ ፡ ምንጮች ፡ አለመኖር ፡ የትምህርቱ ፡ ዓይነት ፡ አስቸጋሪነትና ፡ ሕጉን ፡ ከሀገር ፡ ችግር ፡ ጋር ፡ እያያያዙ ፡ ማስፋፋት ፡ አስፈላጊነት ፡ አንድ ፡ አስተማሪ ፡ ከአንድ ፡ የትምህርት ፡ ዓይነት ፡ በላይ ፡ ሊያስተምርና ፡ ሊያስፋፋ ፡ ይችላል ፡ ተብሎ ፡ ስለማይገመት ፡ ነው ። ሦስተኛ ፡ መሠረታዊ ፡ ውሳኔ ፡ የትምህርት ፡ ቤታችንን ፡ ግንኙነትና ፡ ተጨማሪ ፡ አስተማሪዎችን ፡ መቅጠርያ ፡ ምንጮች ፡ ለማስፋፋት ፡ መጣር ፡ ነበር ። የምናስተምረው ፡ በእንግሊዝኛ ፡ ሆኖ ፡ የሚያስፈልጉን ፡ አስተማሪዎች ፡ ግን ፡ በአውሮጳ ፡ አሕጉር ፡ ሕግ ፡ የሰለጠኑ ፡ መሆን ፡ አለባቸው ። አራተኛው ፡ ውሳኔ ፡ በሌሎቹ ፡ ውሳኔዎች ፡ ምክንያት ፡ የመጣ ፡ ሲሆን ፡ እስከተቻለን ፡ ድረስ ፡ ተጨማሪ ፡ የሚሆኑ ፡ የውጭ ፡ የገንዘብ ፡ እርዳታዎችን ፡ መፈለግ ፡ ነበር ።

በሁለተኛው ፡ ዓመት ፤ የአዳዲስ ፡ መምህራን ፡ ከካናዳ ፡ ከእንግሊዝና ፡ ከአውሮጳ ፡ መምጣት ፡ የትምህርት ፡ ቤቱን ፡ መምህራን ፡ ብዛት ፡ እስከ ፡ አሥራ ፡ ሁለት ፡ አደረሰው ። ከፎርድ ፡ የበጎ ፡ አድራጎት ፡ ድርጅትም ፡ ለሁለተኛ ፡ ጊዜ ፡ የገንዘብ ፡ ልግስና ፡ ተደረገልን ። የእንግሊዝ ፡ የፈረንሳይና ፡ የቤልጅግ ፡ መንግሥትም ፡ አስተማሪዎችን ፡ በራሣቸው ፡ ኪሳራ ፡ በመላክና ፡ የመጻሕፍት ፡ ስጦታ ፡ በማበርከት ፡ ረዱን ። ብዙ ፡ ትናንሽ ፡ የበጎ ፡ አድራጎት ፡ ድርጅቶችና ፡ የግል ፡ ጠበቃዎች ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍታችንን ፡ ለማዳበርና ፡ የተማሪዎች ፡ የጥናትና ፡ ምርምር ፡ ፕሮግራም ፡ በሚገባ ፡ እንዲካሄድ ፡ ይረዳ ፡ ዘንድ ፡ ፲ ፡ ሺ ፡ ብር ፡ (አሥር ፡ ሺ ፡ የአሜሪካን ፡ ብር) ፡ አበረከቱልን ፤ ኒው ፡ ወርልድ ፡ ፋውንዴሽን ፡ የሚባለው ፡ የበጎ ፡ አድራጎት ፡ ድርጅትም ፡ ለቤተ ፡ መጻሕፍታችን ፡ መርጃ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ፭ ፡ ሺ ፡ ብር ፡ (አምስት ፡ ሺ ፡ የአሜሪካን ፡ ብር) ፡ አበረከተ ። ከጀርመን ፡ ሪፐብሊክና ፡ ከዩ ፡ ኤስ ፡ ኤ ፡ አይ ፡ ዲ ፡ እርዳታ ፡ ለማግኘት ፡ ንግግር ፡ ተጀምሮ ፡ ንግግሩ ፡ በሦስተኛው ፡ ዓመት ፡ ፍሬ ፡ አስገኝቷል ።

አስተማሪዎች ፡ በመቅጠር ፡ ረገድ ፡ ከማጊል ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ ጋር ፡ የተመሠረተው ፡ ግንኙነት ፡ ከማጊል ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ ጐረቤት ፡ ከምንትራል ፡ ዩኒቨርሲቲም ፡ አንድ ፡ አስተማሪ ፡ ለመቅጠርና ፡ ከሌሎችም ፡ የኪውቤክ ፡ ዩኒቨርሲቲዎች ፡ ጋር ፡ ተጨማሪ ፡ መግባባትና ፡ ህበረት ፡ ለመመሥረት ፡ አበቃን ። ኪውቤክ ፡ እንደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ድብልቅ ፡ የሆነ ፡ ሕግ ፡ ስላላት ፡ ይህ ፡ መግባባት ፡ ለኢትዮጵያ ፡ የተለየ ፡ ጥቅም ፡ ይሰጣል ። የተባበረው ፡ የአሜሪካ ፡ መንግሥት ፡ የሰላም ፡ ጓድ ፡ ድርጅት ፡ እንደልባችን ፡ ልንመርጥ ፡ የምንችልበት ፡ የብዙ ፡ መምህራን ፡ <u>ማግኛ ፡ መማሪያ</u> ፡ ሆኖ ፡ ለማገልገል ፡ ተስማምቷል ።

ወደ ፡ ሁለተኛው ፡ ዓመት ፡ መጨረሻ ፡ ላይ ፡ ተጨማሪ ፡ የኤል ፡ ኤል ፡ ቢ ፡ የሰርቲፊኬትና ፡ የዲፕሎማ ፡ ተማሪዎች ፡ መዝገብን ፡ በተጨማሪም ፡ በአሥመራ ፡ ከተማ ፡ ለአቃቤ ፡ ሕጎች ፡ ለዳኞችና ፡ ለጠበቆች ፡ የሚሆን ፡ ለምስክር ፡ ወረቀት ፡ (ሰርቲፊኬት) ፡ የሚያበቃ ፡ ትምህርት ፡ ለመስጠት ፡ የማታ ፡ የሕግ ፡ ት/ቤት ፡ በመክፈት ፡ ላይ ፡ ነበርን ። ሦስተኛው ፡ ዓመት ፡ መጀመሪያ ፡ ለዲፕሎማው ፡ ፕሮግራም ፡ ከተቀበልናቸው ፡ ተማሪዎች ፡ ከፊሉ ፡ በአማርኛ ፡ እንዲማሩ ፡ በማድረግ ፡

የዲፕሎማን ፡ ፕሮግራም ፡ አስፋፋን ፤ የዚህም ፡ ፕሮግራም ፡ አስተማሪዎች ፡ ለማስተማሪያና ፡ ለሕግ ፡ መሠረታዊ ፡ ሰነዶች ፡ ይሆኑ ፡ ዘንድ ፡ ጽሑፎችን ፡ ወደ ፡ አማርኛ ፡ መተርጐም ፡ ጀመሩ ። በተጨማሪም ፡ ስለ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ለመማር ፡ የሚፈልጉትን ፡ የፓርላማ ፡ ባልደረባዎች ፡ ለማስተማር ፡ ስለተጠየቅን ፡ በእንግሊዝኛና ፡ በአማርኛ ፡ ሆኖ ፡ ልዩ ፡ የሕገ ፡ መንግሥት ፡ የመሠረታዊ ፡ ሃሳብ ፡ ትምህርት ፡ ፕሮግራም ፡ ተጀመረ ። የአሥመራው ፡ ፕሮግራም ፡ በአንድ ፡ ክፍል ፡ አደገ፤ አስተማሪዎቹም ፡ ሦስት ፡ ሲሆኑ ፡ አንድ ፡ የሙሉ ፡ ጊዜ ፡ ሁለቱ ፡ የግሚስ ፡ ጊዜ ፡ አስተማሪዎች ፡ ናቸው ። እንዲሁም ፡ ከትምህርት ፡ ቤቱ ፡ ጋር ፡ የተያያዘ ፡ ትንሽ ፡ የሕግ ፡ ቤት ፡ መጻሕፍት ፡ ተከፍቷል ። በጠቅላላው ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ በአዲስ ፡ አበባና ፡ በአሥመራ ፡ የምንሰጠውን ፡ ትምህርት ፡ የሚሳተፉ ፡ ፳፻፶ ፡ ሰዎች ፡ ተመዝግበው ፡ ነበር ።

በመጀመሪያዎቹ ፡ ሁለት ፡ ዓመታት ፡ ውስጥ ፡ ትምህርት ፡ ቤቱ ፡ ምርመራና ፡ ጥናት ፡ የተደረገባቸውን ፡ ጉዳዮች ፡ መታተም ፡ ማስፋፋት ፡ ጀመረ ። ዓላማውም ፡ በተቻለን ፡ መጠን ፡ (፩) በሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤቱ ፡ ውስጥ ፡ ማስተማሪያ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ መሠረታዊ ፡ የሆኑ ፡ ጽሑፎች ፡ ለማስገኘትና ፡ (፪) ስለ ፡ ዘመናዊው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ የሚገልጹና ፡ የሚያብራሩ ፡ ጽሑፎች ፡ ለማበርከት ፡ ነበር ። ከፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ ጋር ፡ በመተባበር ፡ በሰኔ ፡ ወር ፡ በአማርኛና ፡ በእንግሊዝኛ ፡ የሚታተመውን ፡ <u>የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ መጽሔት ፡</u> የመጀመርያ ፡ እትም ፡ አሳተምን ፤ መጀመርያ ፡ ጊዜም ፡ የሕግ ፡ ሥራን ፡ ለማደርጀት ፡ የታተሙ ፡ ምርጥ ፡ ፍርዶችንና ፡ ስለ ፡ ጊዜው ፡ ሕጋዊ ፡ ችግር ፡ የተጻፉ ፡ አንቀጾችን ፡ አበረከተ ። ከመጽሔቱም ፡ ሌላ ፡ ሌሎች ፡ መጻሕፍት ፡ ታተሙ ፤ የፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ውሳኔዎችን ፡ የያዘ ፡ ትልቅ ፡ ፋይል ፡ ተሰበሰበ ፡ የሌሎች ፡ ጽሑፎች ፡ ትርጉምም ፡ ተጀመረ ።

ከሐምሌ ፡ ወር ፡ <u>፲፱፻፶፰</u> ፡ እስከ ፡ ሐምሌ ፡ ወር ፡ <u>፲፱፻፶፯</u> ፡ ባለው ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ የቤት ፡ መጻሕፍታችን ፡ እድገት ፡ ከምንም ፡ ተነስቶ ፡ እስከ ፡ ፺፯ ፡ ያህል ፡ መጻሕፍት ፡ አደረሰ ። ይኸም ፡ እድገት ፡ የተቃናው ፡ ለቤት ፡ መጻሕፍቱ ፡ "በውጭ ፡ አገር ፡ እንደሚኖር ፡ ሃላፊ" ፡ አማካሪና ፡ የመጻሕፍት ፡ ገዥ ፡ በመሆን ፡ በጣሩትና ፡ በደከሙት ፡ የራትገርስ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ ባልደረባ ፡ በሆኑት ፡ በፕሮፌሰር ፡ አልበርት ፡ ብሎሽተይን ፡ ብርታት ፡ ነው ። ፕሮፌሰር ፡ ብሎሽተይን ፡ ሥራቸውን ፡ በሚገባ ፡ በማከናወናቸው ፡ ባ<u>፲፱፻፶፯</u> ፡ ዓ፡ ም. ለቤት ፡ መጻሕፍታችን ፡ የሙሉ ፡ ጊዜ ፡ ሠራተኛና ፡ ሰፋ ፡ ያለ ፡ ክፍል ፡ አስፈልገን ። ይኸም ፡ ባ<u>፲፱፻፶፰</u> ፡ ዓ. ም. ተከናወነ ። አሁን ፡ ቤት ፡ መጻሕፍታችን ፡ የሙሉ ፡ ጊዜ ፡ ሠራተኞች ፡ ችሎታ ፡ ያላቸው ፡ የቤተ ፡ መጻሕፍቱ ፡ ሹምና ፡ ጠንካራ ፡ ሠራተኛ ፡ የሆነው ፡ የመምህራን ፡ ኰሚቴ ፡ በሚያደርጉት ፡ ጥረት ፡ በሰፊው ፡ ተሻሽሏል ።

በእውነቱ ፡ የትምህርት ፡ ቤታችን ፡ የሥራ ፡ ማካሄጃ ፡ ሥፍራ ፡ መስፋፋትም ፡ ሊጠቀስ ፡ የሚገባ ፡ ነው ። መጀመርያ ፡ ዱክ ፡ ቤት ፡ ቀጥሎም ፡ የንጉሡ ፡ ነገሥቱ ፡ ልዩ ፡ ካቢኔ ፡ የነበረው ፡ የሕግ ፡ ሕንጻ፡በክረምቱ፡ወቅት፡ቤሐምሌ፡ወር ፡ <u>፲፱፻፶፭</u> ዓ. ም. በገባንበት ፡ ጊዜ ፡ ባዶ ፡ ያልተጠረገና ፡ በመጠኑም ፡ የሚያስፈራ ፡ ነበር ። አሁን ፡ ግን ፡ በሙሉ ፡ እንጠቀምበታለን ፤ ከጧቱ ፡ ፪ ፡ ሰዓት ፡ ከ፴፭ ፡ እስከ ፡ ምሽቱ ፡ ፫ ፡ ሰዓት ፡ ድረስ ፡ ምንም ፡ ያህል ፡ ሳይቋረጥ ፡ ትምህርት ፡ ይሰጥበታል ። ከምድር ፡ ቤቱ ፡ አብዛኛው ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ ሆኗል ። በዚሁ ፡ ሕንፃ ፡ አጠገብ ፡ ያለውን ፡ ሌላ ፡ ሕንጻና ፡ ቀድሞ ፡ የማኅበራዊ ፡ ሥራ ፡ ት/ቤት ፡ ይጠቀምበት ፡ የነበረውን ፡ ሕንጻ ፡ ተረክበናል ። በባዶ ፡ ሕንጻ ፡ ጀመርን ፡ በሚመጣው ፡ ዓመት ፡ ግን ፡ በዚሁ ፡ ግቢ ፡ ውስጥ ፡ ራሱን ፡ የቻለ ፡ ግቢ ፡ ይኖረናል ።

በሦስተኛው ፡ ዓመታችን ፥ በአዲስ ፡ አበባና ፡ በአሥመራ ፡ ፲፯ ፡ የሙሉ ፡ ጊዜ ፡ አስተማሪዎች ፤ (ሦስቱ ፡ ለአንድ ፡ የትምህርት ፡ ወራት ፡ (ሴምስተር) ብቻ) ፡ ዘጠኝ ፡ የገሚስ ፡ ጊዜ ፡ አስተማሪዎችና ፡ አንድ ፡ በፈቃድ ፡ ላይ ፡ ያለ ፡ በጠቅላላው ፡ ፳፯ ፡ አስተማሪዎች ፡ ነበሩን ።

የትምህርት ፡ ፕሮግራማችንም ፡ የሚከተሉትን ፡ የያዘ ፡ ነበር ፡—

ሦስት ፡ የኤል ፡ ኤል ፡ ቢ ፡ (የሕግ ፡ ዲግሪ) ፡ ክፍሎች ፡ (ሙሉ ፡ ጊዜ ፡ ተማሪዎች) ፡ አንድ ፡ የኤል ፡ ኤል ፡ ቢ ፡ (የሕግ ፡ ዲግሪ) ፡ ክፍል ፡ (የማታ ፡ (የከፊል ፡ ጊዜ) ፤ ከሙሉ ፡ ጊዜው ፡ ፕሮግራም ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ ሆኖ ፥ ነገር ፡ ግን ፡ የአራት ፡ ዓመት ፡ ፕሮግራም ፡ ነው ፤ ተማሪዎቹ ፡ የሚወስዱት ፡ ፈተና ፡ ከሙሉ ፡ ጊዜ ፡ ተማሪዎች ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ ሆኖ ፡ የሚወስደውም ፡ የተፈታኞቹ ፡ ስም ፡ ሳይገለጽ ፡ ነው ።)

ሦስት ፡ የዲፕሎማ ፡ ክፍሎች ፡ (ሁለቱ ፡ የሚማሩት ፡ በእንግሊዝኛ ፡ ሲሆን ፥ አንዱ ፡ ግን ፡ በአማርኛ ፡ ነው) ፤ ሦስት ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ፡ (የሰርቲፊኬት) ፡ ክፍሎች ፡ (ሁለቱ ፡ ክፍሎች ፡ አሥመራ ፡ ሆነው ፡ ትምህርቱ ፡ የሚሰጣቸው ፡ በእንግሊዝኛ ፡ ነው ፤ አንዱ ፡ ክፍል ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ሆኖ ፡ ትምህርት ፡ የሚሰጠው ፡ በአማርኛ ፡ ነው) ፤ አንድ ፡ የሕገ ፡ መንግሥት ፡ ትምህርት ፡ የሚከታተል ፡ የልዩ ፡ ምስክር ፡ ወረቀት ፡ ክፍል ፡ (በነርሱ ፡ አመልካችነት ፥ ለፓርላማ ፡ ባልደረቦች ፡ የታቀደ) ።

በጠቅላላ ፥ ባለፈው ፡ የትምህርት ፡ ዓመት ፡ መጀመሪያ ፡ ወደ ፡ ፩፻፶ ፡ ገደማ ፡ የሚሆኑ ፡ ተማሪዎች ፡ ነበሩ ፤ ከነርሱም ፥ በግምት ፡ ፺ ፡ የሚሆኑት ፡ ኤል ፡ ኤል ፡ ቢ ፡ ዲግሪ ፡ የሚያስገኘውን ፡ ትምህርት ፡ ይከታተሉ ፡ ነበር ፡፡ የቀሩት ፥ እዚህና ፡ አስመራ ፡ ያለውን ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ፡ የሚያስገኘውን ፡ ትምህርት ፡ ይከታተሉ ፡ ነበር ፡፡ ከነዚህ ፡ ተማሪዎች ፡ ውስጥ ፥ ቢያንስ ፡ ከሙቶ ፡ ፸፭ቱ ፡ ዳኞች ፡ ዓቃቤ ፡ ሕጎች ፡ ፖሊሶች ፥ የመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፥ የጦር ፡ መኰንኖች ፡ ወይም ፡ የፓርላማ ፡ ባልደረቦች ፡ ነበሩ ። ጠበቃዎችም ፡ ብዙ ፡ ተመዝግበው ፡ ነበር ።

ከአርትስ ፡ ፋኩልቲ ፡ ጋር ፡ በመተባበር ፡ ተማሪዎችን ፡ ወደ ፡ ሕግ ፡ ት/ቤት ፡ ለማግባት ፡ የሚያዘጋጅ ፡ ፕሮግራም ፡ ተቋቁሟል ፤ አሁን ፡ በአርትስ ፡ ፋኩልቲ ፡ (በንግድ ፡ ሥራ ፡ ፋኩልቲ ፡ ያሉትም) ፡ የሚገኙ ፡ ወደ ፡ ሕግ ፡ ፋኩልቲ ፡ ለማግባት ፡ የሚፈልጉ ፡ ተማሪዎች ፡ የኰሌጅ ፡ የመጀመርያ ፡ ዓመታቸውን ፡ እንደጨረሱ ፥ ለእዚሁ ፡ ፕሮግራም ፡ መመዝገብ ፡ ይኖርባቸዋል ። ሁለተኛ ፡ ዓመት ፡ ሲገቡም ፡ የመረጥንላቸውን ፡ ትምህርት ፡ ዓይነቶች ፡ ይከታተላሉ ፤ ከነዚህም ፡ የትምህርት ፡ ዓይነቶች ፡ ለመጀመርያ ፡ ያህል ፡ የሕግ ፡ ሥርዓት ፡ ትምህርት ፥ የሕግ ፡ የአጻጻፍ ፡ ትምህርትና ፡ ፈረንሳይኛ ፡ ይገኙባቸዋል ። ተማሪዎች ፡ ፋኩልቲአችን ፡ ሊገቡ ፥ የሚችሉት ፡ የሕግ ፡ ፋኩልቲን ፡ መግቢያ ፡ ፕሮግራም ፡ ካጠናቀቁ ፡ በኋላ ፡ ነው ። ለሚመጣው ፡ ዓመት ፡ ፕሮግራሙ ፡ በርከት ፡ ያለ ፡ የሕግ ፡ ትምህርትና ፡ ጠለቅ ፡ ያለ ፡ የፈረንሳይኛ ፡ ትምህርትን ፡ ይይዛል ። በዚህ ፡ ዓመት ፡ በሕግ ፡ ፋኩልቲ ፡ መግቢያ ፡ ፕሮግራም ፡ ውስጥ ፡ ፴ ፡ ተማሪዎች ፡ ተመዝግበዋል ፤ ለወደፊቱም ፡ ወደኛ ፡ ለሚመጡ ፡ ተማሪዎች ፡ ዋና ፡ ምንጭ ፡ ይሆኑናል ፡ ብለን ፡ እንተማመንበታለን ።

ፋኩልቲው ፡ የያንዳንዱን ፡ ተማሪ ፡ የጽሑፍ ፡ ሥራ ፡ ከትምህርቱ ፡ አቋም ፡ ከፍተኛ ፡ ክፍል ፡ የያዘ ፡ መሆኑን ፡ ተማሪዎቹ ፡ በደንብ ፡ እንዲረዱት ፡ ሙከራውን ፡ ቀጥሏል ። የመጀመርያ ፡ ዓመት ፡ የኤል ፡ ኤል ፡ ቢ ፡ ዲግሪ ፡ ተማሪዎች ፡ ዓመቱን ፡ በሙሉ ፡ አጫጭር ፡ ፕሮብሌሞችን ፡ የመተንተን ፡ ተግባር ፡ ይሰጣቸዋል ። የሁለተኛ ፡ ዓመት ፡ ተማሪዎች ፡ ረዘም ፡ ያሉ ፡ ጽሑፎችን ፡ ይጽፋሉ ፤ በተጨማሪም ፡ በብዙ ፡ የትምህርት ፡ ዓይነቶች ፡ ውስጥ ፡ የሕግ ፡ ማርቀቅ ፡ ልምምድ ፡ ያደርጋሉ ። እያንዳንዱ ፡ የመጨረሻ ፡ ዓመት ፡ ተማሪ ፡ ዓመቱን ፡ ሙሉ ፡ አንድ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ የጥናትና ፡ የምርምር ፡ ጽሑፍ ፡ ይደርሳል ።

ይኸም ፡ ጽሑፍ ፡ (ቲሲስ) ፡ በመጨረሻ ፡ የሚሰጠው ፡ ዋጋ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ነው ። ይህ ፡ ፕሮግራም ፡ ከትንሽ ፡ ማሻሻልና ፡ ማስፋፋት ፡ ጋር ፡ ለሚመጣው ፡ ዓመት ፡ ይቀጥላል ።

የፋኩልቲው ፡ የምርምር ፡ ኮሚቴ ፡ የምርምር ፡ ፕሮግራማችንን ፡ ማስፋፋት ፡ ቀጠለ ። ሁለት ፡ መጽሐፎች ፡ (የፕሮፌሰር ፡ ሬደን ፡ ሲጋል ፡ ፎርም ፡ ቡክ ፡ እና ፡ የዶክተር ፡ ቫንደርሊንደን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ምንጮች ፡) ታትመዋል ፤ ሌሎች ፡ ሁለት ፡ መጻሕፍትም ፡ በማተሚያ ፡ ቤት ፡ ናቸው ። በኛ ፡ ጥፋት ፡ ሳይሆን ፡ በማተሚያ ፡ ቤት ፡ መዘግየት ፡ ምክንያት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ መጽሔት ፡ ታትሞ ፡ ይወጣል ፡ በተባለው ፡ ቀን ፡ ሳይወጣ ፡ ዘግይቷል ፤ ይሁን ፡ እንጂ ፡ በኔ ፡ አስተያየት ፡ በውስጡ ፡ ያሉት ፡ ጽሑፎች ፡ መጽሔቱ ፡ የሕግ ፡ ሞያተኞችን ፡ የአዋቂዎች ፡ የሃሳብ ፡ ማስፈሪያ ፡ እንደመሆኑ ፡ መጠን ፡ ከጊዜ ፡ ወደ ፡ ጊዜ ፡ እየተሻሻለ ፡ መሄዱን ፡ ያሳያሉ ።

ቤተ ፡ መጻሕፍታችን ፡ በመጻሕፍት ፡ ብዛትም ፡ ሆነ ፡ በክፍል ፡ መስፋፋት ፡ እያደገ ፡ ሂዷል ። ብዙዎች ፡ የምድር ፡ ቤት ፡ ክፍሎች ፡ ከተለወጡና ፡ ከታደሱ ፡ በኋላ ፡ ለቤተ ፡ መጻሕፍቱ ፡ ተደርበዋል ።

ባለፈው ፡ ዓመት ፡ ፋኩልቲው ፡ የተማሪዎች ፡ የእረፍት ፡ ጊዜ ፡ ሥራ ፡ ፕሮግራም ፡ ጀመረ ። ተማሪዎች ፡ በብዙ ፡ ዓይነት ፡ ውጥኖች ፡ ሲሠሩ ፡ ቆይተዋል ፤ ከነዚህም ፡ ሥራዎች ፡ ውስጥ ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ ውሳኔዎችን ፡ መተርጐም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ መጽሔት ፡ አንቀጾችን ፡ መተርጐም ፡ እየዞሩ ፡ ስለአንዳንድ ፡ ጉዳዮች ፡ ጥናት ፡ ማድረግና ፡ ከአስተማሪዎች ፡ የተሰጡ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሥራዎች ፡ ይገኙባቸዋል ። የእረፍት ፡ ጊዜ ፡ ያለ ፡ ሞያ ፡ ማለፍ ፡ የለበትም ፡ ብለን ፡ እናምናለን ፤ ጊዜው ፡ ጠቃሚ ፡ ምርምር ፡ ሊደረግበትና ፡ ተጨማሪ ፡ ንባብና ፡ ጥናት ፡ በይበልጥ ፡ ሊዘወተርበት ፡ የሚገባ ፡ ጊዜ ፡ ነው ። የሕግ ፡ ሞያተኞችን ፡ ለማስተማር ፡ አምስት ፡ የዩኒቨርሲቲ ፡ ዓመት ፡ በጣም ፡ ያጠረ ፡ ጊዜ ፡ ነው ። የሦስት ፡ ወር ፡ ጊዜ ፡ ዋጋ ፡ አልባ ፡ ማጥፋት ፡ ሞኝነት ፡ ይመስላል ። የዕረፍት ፡ ጊዜ ፡ ሥራ ፡ በዚሁ ፡ ዓመትም ፡ ይቀጥላል ። በተጨማሪም ፡ በአንዳንድ ፡ በተመረጡ ፡ ትምህርቶች ፡ ተጨማሪ ፡ የንባብና ፡ ጥናት ፡ ፕሮግራም ፡ ለማስፋፋት ፡ ተስፋ ፡ እናደርጋለን ።

የሕግ ፡ ተማሪዎች ፡ ማኅበር ፡ ብዙ ፡ ጠቃሚ ፡ የሆኑ ፡ ፕሮግራሞችን ፡ አከናውኗል ፤ በቴሌቭዥን ፡ "እናንተው ፡ ፍረዱ" ፡ የሚባል ፡ በሕዝብ ፡ አድናቆት ፡ ያገኘ ፡ ፕሮግራምን ፡ አካሂዷል ፡ ሌላ ፡ የማኅበሩ ፡ ጠቃሚ ፡ ፕሮግራም ፡ "የሕግ ፡ ተማሪዎች ፡ ቤት" ፡ ሥራ ፡ እንዲጀመር ፡ መድከም ፡ ነበር ። የተማሪዎቻችን ፡ መኖሪያ ፡ ቤት ፡ አኳኋን ፡ በጣም ፡ የሚያሳዝን ፡ ነው ። ከሌሎቹ ፡ ምክንያቶች ፡ ሌላ ፡ ይህ ፡ አኳኋን ፡ የትምህርትን ፡ ደረጃና ፡ የሥራን ፡ መንፈስ ፡ የሚጐዳ ፡ ነው ።

የሕግ ፡ ሞያተኞች ፡ ሕብረት ፡ እንዲስፋፋ ፡ የሚረዳንን ፡ በጣም ፡ ለተቸገሩ ፡ ተማሪዎችም ፡ መኖሪያ ፡ የሚሆን ፡ ቤት ፡ ማግኘት ፡ ለእድገታችን ፡ በጣም ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ። የሕግ ፡ ትምህርት ፡ "በሕግ ፡ ውስጥ ፡ መስጠም" ፡ መሆን ፡ አለበት ፤ የሕግ ፡ ተማሪዎችም ፡ የሚበሉት ፡ የሚተነፍሱትም ፡ ሕግን ፡ መሆን ፡ አለበት ፤ በሕግም ፡ ውስጥ ፡ መኖር ፡ አለባቸው ። ይኸም ፡ እንዲሆን ፡ መኖር ፡ ያለባቸው ፡ በሕግ ፡ ሞያ፡ የተራቀቁ ፡ የሥራ ፡ አባሎቻቸውን ፡ ሊያገኙ ፡ በሚችሉበት ፡ ቦታ ፡ ነው ። ሳምንትን ፡ ሙሉ ፡ በቀን ፡ ፳፬ ፡ ሰዓት ፡ ሊያጠኑ ፡ የሚችሉበት ፡ ቦታ ፡ እንዲኖራቸው ፡ ያስፈልጋል ። ቀጥሎ ፡ እንደሚገለጸው ፡ ሁሉ ፡ "የሕግ ፡ ተማሪዎች ፡ ቤት" ፡ ዕቅድ ፡ የተማሪዎቹ ፡ ራሥን ፡ በራሥ ፡ መርዳት ፡ ፕሮግራም ፡ ሆኖ ፡ በዩኒቨርሲቲው ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ በማኅበሩ ፡ አስተዳዳሪነት ፡ መኖርያ ፡ ቤት ፡ ለማሠራት ፡ የታቀደ ፡ ነው ። የዚህ ፡ ዓላማ ፡ መፈጸም ፡ ለሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤቱ ፡ የወደፊት ፡ ዕድገት ፡ ታላቅ ፡ ተስፋ ፡ ነው ።

ከዚህ ፡ በላይ ፡ ከተጠቀሱት ፡ ጉዳዮች ፡ ዋቂቶቹ ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ በዝርዝር ፡ ተገልጸዋል ።

## የጥናቶችና ፡ የምርምሮች ፡ ማሳተም ፡ ፕሮግራም ።

የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ መጽሔት ፡ በጠቅላላው ፡ ፲፪፻ ፡ ገጽ ፡ የሆኑ ፡ ፪ ፡ ቮልዩሞች ፡ ታትመዋል ፤ እያንዳንዱ ፡ ቮልዩም ፡ ፪ ፡ እትም ፡ አሉት ። መጽሔቱ ፡ የሚታተመው ፡ ከፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ ጋር ፡ በመተባበር ፡ ነው ። በተከበሩ ፡ አቶ ፡ በላቸው ፡ አስራት ፡ ሊቀመንበርነት ፡ የመጽሔቱ ፡ አዘጋጅ ፡ ቦርድ ፡ መሠረታዊ ፡ የሆኑትን ፡ የማተም ፡ ዓላማዎች ፡ (ፖሊሲዎች) ፡ ይወስናሉ ። የመጽሔቱ ፡ ዝግጅት ፡ ሐላፊነት ፡ በመምህራንና ፡ ተማሪ ፡ አዘጋጆዎች ፡ ላይ ፡ ተጥሏል ።

መጻሕፍት ፡—እስካሁን ፡ ሰባት ፡ መጻሕፍት ፡ ታትመዋል ፤ ከነዚህም ፡ ሁለቱ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ የጥናት ፡ ምርምር ፡ ኢንስቲቱት ፡ ጋር ፡ በመተባበር ፡ ስለ ፡ መሬት ፡ ይዞታ ፡ የተዘጋጁ ፡ ናቸው ። የነዚሀ ፡ የሁለቱ ፡ መጻሕፍት ፡ ተከታታይ ፡ ከሪቻርድ፡ ፓንክርስት ፡ የተደረሰው ፡ ሂስትሪ ፡ ኦፍ ፡ ስቴት ፡ ኦውነርሺፕ ፡ ኦፍ ፡ ላንድ ፡ ኤንድ ፡ ላንድ ፡ ቴነር ፡ ኢን ፡ ኢትዮጵያ ፡ የተባለ ፡ መጽሐፍ ፡ አሁን ፡ በመታተም ፡ ላይ ፡ ነው ። በተጨማሪም ፡ በፕሮፌሰር ፡ ኬኔዝ ፡ ሬደን ፡ የተደረሰ ፡ ጽሑፍ ፡ በማተሚያ ፡ ቤት ፡ ይገኛል ።

በማራቢያ ፡ መኪና ፡ የተባዙ ፡ ጽሑፎች ፡—በሕግ ፡ ፋኩልቲ ፡ ለሚሰጠው ፡ ለያንዳንድ ፡ የትምህርት ፡ ዓይነት ፡ ማስተማርያ ፡ ይሆኑ ፡ ዘንድ ፡ በማራቢያ ፡ መኪና ፡ የተባዙ ፡ ጽሑፎች ፡ ተዘጋጅተዋል ። ለሚመጡት ፡ ዓመታት ፡ እነኝህን ፡ ጽሑፎች ፡ ለአትማት ፡ እንደሚበቁ ፡ ማድረግ ፡ ከፋኩልቲው ፡ ዋና ፡ ሥራዎች ፡ አንዱ ፡ ይሆናል ።

በመካሄድ ፡ ላይ ፡ ያሉ ፡ ሌሎች ፡ ውጥኖች ፡—ጠቃሚ ፡ ይሆናሉ ፡ ተብለው ፡ የሚታመኑት ፡ ፍርዶች ፡ በሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ ተቀማጭ ፡ እንዲሆኑና ፡ እንዲሁም ፡ አንዳንዶቹ ፡ በሕግ ፡ መጽሔት ፡ እንዲታተሙ ፡ በረጅሙ ፡ የዕረፍት ፡ ወራት ፡ ተማሪዎች ፡ ሲተረጉሟቸው ፡ ከርመዋል ። ሌላ ፡ ዋና ፡ ውጥን ፡ "ሌክሲኮ ፡ ፕሮዠ" ፡ በሚል ፡ መጠሪያ ፡ የተሰየመው ፡ ውጥን ፡ ነው ። ይህም ፡ ውጥን ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ የሕግ ፡ ቃላትን ፡ በአማርኛ ፡ ትክክለኛ ፡ ትርጉም ፡ ለመ

ስጠት ፣ ባስፈለገ ፡ ጊዜም ፡ አዳዲስ ፡ ቃላትን ፡ በመፍጠር ፡ ችግሩን ፣ ለማስወገድ ፡ የተወሰደ ፡ የመጀመርያ ፡ እርምጃ ፡ ነው ። ተማሪዎች ፡ የፊደልን ፡ ቅደም ፡ ተከተል፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፣ በኢትዮጵያ ፡ ሕጎች ፡ ውስጥ ፡ በአማርኛው ፡ በእንግሊዝ ኛውና ፡ ሲኖርም ፡ በፈረንሳይኛው ፡ ጽሑፍ ፡ አንዱን ፡ ነገር ፡ ለመግለጽ ፣ የተጻፉትን ፡ ቃላት ፡ በመልቀም ፡ "ማውጫ" ፡ በማዘጋጀት ፡ ላይ ፡ ናቸው ። ይኸ ፡ ውጥን፡ ሲያልቅ ፡ ጥናትና ፡ ምርምር ፡ ለሚያደርጉ ፡ ሁሉ ፡ የሕግ ፡ ቃላት ፡ በሦስቱ ፡ ቋንቋ ዎች ፡ ውስጥ ፣ ካንድ ፡ ወደሌላው ፡ እንዴት ፡ እንደሚተረጐሙ ፡ ባጭር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ለማወቅ ፡ ያስችላቸዋል ።

## የቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ ዕድገት ።

፩ ፤ የመጻሕፍት ፡ ብዛት ።

(ሀ) ጠቅላላ ፡ ብዛት ፡ ፳፫ሺ፪፻፳፰ ፡ ቮልዩሞች ፣ (ከነዚሁ ፡ ውስጥ ፡ ሺ፳፻፫ቱ መጽሔቶች ፡ ሲሆኑ ፣ ፯፻፯ዎቹ ፡ የመንግሥት ፡ ሰነዶች ፡ ናቸው) ።

(ለ) ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ጽሑፎች ፡ ብዛት ።

(፩) በቤተ ፡ መጻሕፍቱ ፡ ውስጥ ፡ ፪፻፴ ፡ ቮልዩሞች ፡ አሉን ።
(፪) በመዝገብ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ፵፯ ፡ ቮልዩሞችና ፣ ፪፻፰ ፡ ያልተጠረዙ ፡ ጽሑፎች ፡ አሉን ፤ ከነዚህም ፡ ውስጥ ፡ ሰነዶች ፣ የፍርድ ፡ ውሳኔዎች ፣ የሕግ ፡ ግልባጮችና ፡ ስለ ፡ ሕግ ፡ ትችት ፣ (ሲያንስ) ፡ ነክ ፡ የሆኑ ፡ ጹሑ ፎች ፡ ይገኙባቸዋል ።

፪ ፤ በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ የተቀበልናቸው ፡ ፪፻፷ ።

፫ ፤ ከነሐሴ ፡ ፲፱፻፶፯ ፡ ዓ. ም. ጀምሮ ፡ የተገዙ ፡ (እየተደጋገሙ ፡ የተገዙትን ፡ ሳን ቆጥር) ፡ ሺ፪፻፶ ፡ ቮልዩሞች ።

፬ ፤ ስጦታዎች ።

(ሀ) ከቤልጂግ ፡ መንግሥት ፡ ፹፩ሺ፬፻፲፩ ፡ የቤልጂግ ፡ ፍራንክ ፡ የሚያወጣ ፡ የሕግ ፡ ጽሑፎች ፡ ስጦታ ።

(ለ) ከጀርመን ፡ ፌደራል ፡ ሪፑብሊክ ፡ የ፳ ፡ ቮልዩሞች ፡ ስጦታ ።
(ሐ) ከዓለም ፡ አቀፍ ፡ የሕግ ፡ ሊቃውንት ፡ ኮሚሲዮን ፡ ስለ ፡ ዓለም ፡ አቀፍ ፡ ሕግ ፡ የተጻፉ ፡ የ፳ ፡ መጻሕፍት ፡ ስጦታ ።

(መ) ከኢትዮጵያ ፡ የውጭ ፡ ጉዳይ ፡ ሚኒስቴር ፡ ፭ ፡ ቮልዩም ፡ የዓለም ፡ አቀፍ፡ ፍርድ ፡ ስጦታ ።

(ሠ) ከተባበሩት ፡ መንግሥታት ፡ የአፍሪካ ፡ ኢኮኖሚ ፡ ኮሚሲዮን ፡ ስለ ፡ ኢኮኖሚ ፣ የማሕበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ፕሮብሌሞች ፣ ዓለም ፡ አቀፍ ፡ ሕግ ፣ ዓለም ፡ አቀፍ፡ አስተዳደር ፣ የሰው ፡ መብትና፡ ሌሎችም፡ ጽሑፎች፡ የሚጠቅሱ፡ የሰነዶች፡ ስጦታ።

(ረ) ከኢትዮጵያ ፡ ከፍተኛ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ዳኛ ፡ ደብልዩ ፡ ግራበውስኪ ፡ ከግል ፡ የሕግ ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍታቸው ፡ ፵ ፡ ቮልዩም ፡ ስጦታ ።

ቤተ ፡ መጻሕፍታችን ፡ አሁን ፡ ባለበት ፡ ሁኔታ ፡ ለወደፊቱ ፡ በምንም ፡ ዓይ ነት ፡ በቂ ፡ አይሆንም ። በቂ ፡ ገንዘብ ፡ ብናገኝ ፣ ኢትዮጵያን ፡ በደምብ ፡ የሚያገ ለግል ፣ ለትምህርት ፣ ፕሮግራማችን ፡ ማስፋፊያ ፡ መሠረት ፡ የሚሆን ፣ በተለይም ፡

በአፍሪቃ ፡ የልዩ ፡ ልዩ ፡ ሀገሮችን ፡ ሕጎች ፡ በማመዛዘን ፡ ጥናት ፡ በኩል ፡ የሚያገለግል ፡ የምርምር ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ እናቋቁማለን ። የሕግ ፡ ት/ቤቱን ፡ በጣም ፡ ጥሩ ፡ ለማድረግ ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍታችንን ፡ በጣም ፡ ጥሩ ፡ ማድረግ ፡ አለብን ። ይህን ፡ ሥራ ፡ ከግቡ ፡ ለማድረስ ፡ ለወደፊቱ ፡ በቂ ፡ የሆኑ ፡ የገንዘብ ፡ ምንጮች ፡ መፈለጋችን ፡ አይቀርም ።

<u>የታወቁ ፡ እንግዶችና ፡ የሕግ ፡ ሸንጎዎች ።</u>

በፊት ፡ ለ፭ ፡ ዓመታት ፡ በካርቱምና ፡ በዳርኤሰላም ፡ የሕግ ፡ ፋኩልቴዎች ፡ ያስተምሩ ፡ የነበሩት ፡ አሁን ፡ የቤልፋስት ፡ ኩዊንስ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ አስተማሪ ፡ ፕሮፌሰር ፡ ዊሊያም ፡ ትዋይኒንግና ፡ የሐርባርድ ፡ ሕግ ፡ ት/ቤት ፡ አስተማሪ ፡ ፕሮፌሰር ፡ ሮጀርፌሸር ፡ የውጭ ፡ ገማቾች ፡ ሆነው ፡ ት/ቤቱን ፡ ጐብኝተዋል ። ሁለቱም ፡ ስለ ፡ ትምህርት ፡ አሰጣጥ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓታችን ፡ ስለ ፡ አስተማሪዎች ፡ አቀጣጠራችንና ፡ ስለሌሎችም ፡ ነገሮች ፡ አስተያየታቸውንና ፡ ምክራቸውን ፡ አካፍለውናል ፡ ከአስተያየቶቻቸውም ፡ ጥቂቶቹን ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ አውለናቸዋል ።

ከዛግሬብ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ ፕሮፌሰር ፡ ሚርጃን ፡ ደማሽካ ፡ ለአስር ፡ ቀናት ፡ ያህል ፡ ጐብኝተውናል ፤ በጐብኝታቸውም ፡ ጊዜ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሲያስተምሩ ፡ ሰንብተዋል ፡ ስለ ፡ ሶሽያሊስት ፡ አገሮች ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ አስተሳሰብም ፡ ንግግር ፡ አድርገዋል ። ጉብኝታቸው ፡ እኛን ፡ ከማበረታታቱም ፡ ሌላ ፡ ብዙ ፡ ረድቶናል ።

በፎርድ ፡ ድርጅት ፡ የሚካሄደው ፡ ለአፍሪቃ ፡ የሕግ ፡ ት/ቤቶች ፡ አስተማሪ ፡ በመቅጠርና ፡ ካገር ፡ ውጭ ፡ ያሉትን ፡ አስተማሪዎች ፡ ወጪ ፡ በመቻል ፡ እርዳታ ፡ የሚሰጠው ፡ የሳይለር ፡ ክንውን ፡ አስፈጻሚ ፡ ኮሚቴ ፡ ሊቀመንበርና ፡ የፔንሲልቫንያ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ ዲን ፡ የሆኑት ፡ ዲን ፡ ጀፈርሰን ፡ ፎርድሃም ፡ ለብዙ ፡ ቀናት ፡ ጐብኝተውናል ።

የካርቱም ፡ የሕግ ፡ ፋኩልቲ ፡ ዲን ፡ ዲን ፡ ዛኪ ፡ ሙስጣፋ ፡ በከፊል ፡ ለራሳቸው ፡ ደስታ ፤ በከፊልም ፡ የአፍሪካ ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ ማኅበር ፡ መመሥረትን ፡ ተስፋ ፡ በማድረግ ፡ የኢባደን ፡ ሕግ ፡ አስተማሪዎች ፡ ሰብሰባ ፡ የሰጠው ፡ አስተያየት ፡ በሥራ ፡ ስለሚውልበት ፡ ዘዴ ፡ ለመነጋገር ፡ ለብዙ ፡ ቀናት ፡ ጐብኝተውናል ።

ቀድሞ ፡ የዩ. ሲ. ኤል. ኤ. የአፍሪካ ፡ ጥናት ፡ ፕሮግራም ፡ ሃላፊ ፡ የነበሩት ፡ አሁን ፡ ማከሬሬ ፡ የፖሊቲካል ፡ ሳይንስ ፡ ፕሮፌሰርና ፡ ሊቀመንበር ፡ የሆኑት ፡ ፕሮፌሰር ፡ ጀምስ ፡ ክሌማን ፡ ጐብኝተዉን ፡ ነበር ። በአፍሪቃ ፡ ነጠላ ፡ ፓርቲ ፡ (ማኅበር) ፡ የፖለቲካ ፡ አቋም ፡ ንግግር ፡ አድርገዋል ።

የኮኔክቲኩት ፡ ጠበቆች ፡ ማኅበር ፡ ባልደረባ ፡ የሆኑት ፡ ዶክተር ፡ ሔንሪ ፡ ኤል ፡ ሸፐርድ ፡ በአውሮፓ ፡ በእንግሊዝና ፡ በአሜሪካ ፡ ስለ ፡ ሕግ ፡ ተግባር ፡ እድገት ፡ ንግግር ፡ አደረጉ ።

የአፍሪካ ፡ ዓለም ፡ አቀፍ ፡ ኢንስቲቱት ፡ ስለ ፡ "አፍሪቃ ፡ ሕግ ፡ ዕንስ ፡ ሐሳብና ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት" ፡ በጥር ፡ ወር ፡ ውስጥ ፡ ለአሥር ፡ ቀናት ፡ የጥናት ፡ ጉባኤ ፡ አደረገ ። ከአስተማሪዎች ፡ ከሕግ ፡ ሥራ ፡ ሞያተኞች ፡ ከጠበቆችና ፡ ከአንትሮፖ

ሎጂስቶች ፡ የተውጣጡ ፤ ከአውሮፓ ፡ ከአሜሪካና ፡ ከአፍሪቃ ፡ የመጡ ፡ ፲፰ ፡ ሊቃውንት ፡ የዚህ ፡ ጉባኤ ፡ ተካፋዮች ፡ ሆነው ፡ ነበር ። ከዚሁ ፡ ጋር ፡ በማያያዝ ፡ የአፍሪቃ ፡ ዓለም ፡ አቀፍ ፡ የሕግ ፡ ማኅበር ፡ የዓመት ፡ ጉባኤውን ፡ በፋኩልቴ ያችን ፡ አደረገ ።

የሕግ ፡ ተማሪዎች ፡ ማኅበር ፡ በርከት ፡ ያሉ ፡ የሕግ ፡ ሸንጎዎችና ፡ ንግግሮች ፡ አካሂዷል ፤ ከነዚህም ፡ ጥቂቶቹ ፡ የሮዴሺያ ፡ ፕሮብሌም ፡ ጠበቃን ፡ የማግኘት ፡ ሕገ ፡ መንግሥታዊ ፡ መብትና ፡ የኮንጐ ፡ ሬፑብሊክ ፡ የሕገ ፡ መንግሥት ፡ እድገት ፡ ነበሩ ።

የሕግ ፡ ተማሪዎች ፡ ማኅበር ፡ ከፍተኛው ፡ ፕሮግራም ፡ የሕግ ፡ ት/ቤት ፡ ቀን ፡ ነበር ፤ በዚህ ፡ ዕለት ፡ በዩኒቨርሲቲው ፡ ፕሬዘዳንት ፡ መሪነት ፡ "የሕግ ፡ ተማሪዎች ፡ ቤት" ፡ መሠረት ፡ ተጣለ ። የተከበሩ ፡ አቶ ፡ ማሞ ፡ ታደሰ ፡ የፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ ለተማሪዎቹ ፡ ንግግር ፡ አደረጉ ፤ ተማሪዎቹም ፡ የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ፕሬዘዳንት ፡ ዶክተር ፡ ቡሐጀር ፡ ባስቻሉበት ፡ በቲያትር ፡ መልክ ፡ ችሎት ፡ አሳዩ። ይህ ፡ ሦስተኛው ፡ ዓመታዊ ፡ የሕግ ፡ ት/ቤት ፡ ቀን ፡ ካለፉት ፡ ሁለት ፡ የሕግ ፡ ት/ቤት ፡ ቀኖች ፡ ይበልጥ ፡ እድናቆትን ፡ አግኝቷል ። ለሚመጣው ፡ ዓመት ፡ የቀድሞ ፡ ተማሪዎቻችን ፡ የሚገኙበት ፡ የሕግ ፡ ት/ቤት ፡ ቀን ፡ እንደምናከብር ፡ እተማመ ናለሁ ፤ የሕግ ፡ ት/ቤት ፡ በእድሜ ፡ እያደገ ፡ ሲሄድም ፡ በጣም ፡ ብዙ ፡ የቀድሞ ፡ ተማሪዎች ፡ የሚገኙበት ፡ "የሕግ ፡ ት/ቤት ፡ ቀን" ፡ ለማክበር ፡ እንደምንበቃ ፡ሙሉ ፡ ተስፋ ፡ አለኝ ።

"እናንተው ፡ ፍረዱ" ፡ በተባለው ፡ በቴሌቭዥን ፡ ሲካሄድ ፡ በነበረው ፡ በሕዝብ ፡ ተወዳጅነትን ፡ ባስገኘው ፡ ፕሮግራምም ፡ ተማሪዎች ፡ ተሳትፈዋል ። እነ ዚሁ ፡ የይግባኝ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ክርክሮች ፡ የተዘጋጁት ፡ በፋኩልቲ ፡ ባልደረባ ፡ አማካሪነት ፡ በሕግ ፡ ተማሪዎች ፡ ማኅበር ፡ ተባባሪነት ፡ ሲሆን ፡ የታቀዱት ፡ ሕጋዊ ፡ ክርክርና ፡ የሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓትን ፡ በማሳየት ፡ ሕዝቡን ፡ ሕግ ፡ ለማስ ተማር ፡ ነው ።

## የአስመራ ፡ የማታ ፡ ትምህርት ፡ ፕሮግራም ።

ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለው ፡ ጽሑፍ ፡ የተወሰደው ፡ ከሚስተር ፡ ኖርማን ፡ መት ዘር ፡ የአስመራ ፡ የማታ ፡ ት/ቤት ፡ አስተማሪ ፡ መግለጫ ፡ ነው ።

በ፲፱፻፶፮ ፡ ዓ. ም. በአስመራ ፡ ስለ ፡ ሕግ ፡ የማታ ፡ ትምህርት ፡ ፕሮግራም ፡ አስፈላጊነት ፡ ጥናት ፡ ለማድረግ ፡ ወደ ፡ አስመራ ፡ ተላክሁ ። ከጠቅላይ ፡ አቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ከጠቅላይ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ምክትል ፡ አፈንጉሥ ፡ ከከፍ ተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ፕሬዘዳንትና ፡ ከአስመራ ፡ በኢ. ን. ነ. የፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ ሥራ ፡ አስኪያጅ ፡ ጋር ፡ ንግግር ፡ ጀመርኩ ። ሁሉም ፡ የማታ ፡ ትምህርት ፡ ፕሮ ግራም ፡ መከፈት ፡ አስፈላጊ ፡ መሆኑንና ፡ የተቻላቸውንም ፡ ያህል ፡ ለመርዳት ፡ መስማማታቸውን ፡ ገለጹልኝ ።

ተሰብስበን ፡ ከተወያየንበት ፡ በኋላ ፡ በኅዳር ፡ ፳፱ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፯ ፡ ዓ. ም. የማታ ፡ ትምህርት ፡ ፕሮግራሙን ፡ ለመክፈት ፡ ለጊዜው ፡ ዝግጅት ፡ አደረግን ። የፕሮግራሙ ፡ ዋና ፡ ዓላማ ፡ ከሕግ ፡ ሥራ ፡ ጋር ፡ ግንኙነት ፡ ያላቸውን ፡ የመንግ ሥት ፡ ሠራተኞች ፡ ለማስተማር ፡ ስለ ፡ ነበር ፡ በኤርትራ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ የፍ ርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ ሥራ ፡ አስኪያጅ ፡ የመማር ፡ ፍላጎትንና ፡ የእንግሊዝኛ ፡ ችሎታ፡

ያላቸውን ፡ ሁሉ ፡ በፕሮግራሙ ፡ ተሳታፊ ፡ ለመሆን ፡ ይመዘገቡ ፡ ዘንድ ፡ ጠየቋቸው ። የመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ ከየመሥሪያ ፡ ቤታቸው ፡ ፈቃድ ፡ ተሰጥቷቸው ፡ ትምህርቱ ፡ ከሰዓት ፡ በኋላ ፡ እንዲሰጥ ፡ ተወሰነ ። መሥሪያ ፡ ቤቶችም ፡ እያንዳንዱን ፡ ተማሪ ፡ ለመማሪያ ፡ የሚከፍለውን ፡ ገንዘብ ፡ ከደመወዙ ፡ እየቆረጡ ፡ በመስጠት ፡ ፋኩልቲው ፡ ገንዘቡን ፡ በቀላል ፡ መንገድ ፡ እንዲያገኝ ፡ አስቻሉት ።

በኅዳር ፡ ወር ፡ በሁለተኛው ፡ ሳምንት ፡ በአስመራ ፡ ጋዜጦች ፡ ውስጥ ፡ በኅዳር ፡ ፪ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፯ ፡ ዓ. ም. የማታ ፡ ትምህርት ፡ ፕሮግራም ፡ መከፈቱንና ፡ ፍላጐት ፡ ያላቸው ፡ ሰዎች ፡ አቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ የማታ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ እየሄዱ ፡ መመዝገብ ፡ መቻላቸውን ፡ የሚገልጽ ፡ ማስታወቂያ ፡ ታተመ ። ውጤቱም ፡ በጣም ፡ አጥጋቢ ፡ ሆኖ ፡ አገኘነው ። ክፍል ፡ ለመጀመር ፡ ቢያንስ ፡ ፴ ፡ ተማሪዎች ፡ ያስፈልጉናል ፡ ብለን ፡ ወስነን ፡ ነበር ። በጠቅላላ ፡ ፹፪ ፡ ተማሪዎች ፡ ሲመዘገቡ ፡ ለመጀመሪያ ፡ የክፍል ፡ ጊዜ ፡ ፷፯ ፡ ተገኝተው ፡ ነበር ።

ትምህርቱ ፡ በኅዳር ፡ ፳፫ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፯ ፡ ዓ. ም. ተጀመረ ። ለመጀመሪያው ፡ የትምህርት ፡ መንፈቅ ፡ የተሰጠው ፡ ትምህርት ፡ የወንጀል ፡ ሕግና ፡ የኢትዮጵያ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ነበር ። በሁለተኛው ፡ የትምህርት ፡ መንፈቅ ፡ የተሰጠው ፡ ትምህርት ፡ የኢትዮጵያ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ነበር ። እነዚህ ፡ ትምህርቶች ፡ መጀመሪያ ፡ የተሰጡበት ፡ ምክንያት ፡ አብዛኛዎቹ ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ ተማሪዎች ፡ ሥራቸው ፡ የወንጀል ፡ ሕግና ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ጠቀስ ፡ ስለነበረ ፡ ነው ።

ወደ ፡ ፲፱፻፶፯ ፡ ዓ. ም. መጨረሻ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ለመስከረም ፡ ፲፱፻፶፰ ፡ ዓ. ም. አዲስ ፡ ክፍል ፡ ለመጀመር ፡ እቅዳን ፡ እንደሆነ ፡ ለማወቅ ፡ ጠየቁኝ ። ስለዚህ ፡ ነገር ፡ እኔም ፡ ከሊቃቤ ፡ ሕጉና ፡ ከከፍተኛ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ፕሬዘዳንት ፡ ጋር ፡ ተነጋገርኩ ። አዲስ ፡ ክፍል ፡ የመጀመሩን ፡ አስፈላጊነት ፡ ይመዘገባሉ ፡ ከሚባለው ፡ ግምት ፡ ጋር ፡ አስተያየት ፡ መወሰኑ ፡ በጣም ፡ አስቸጋሪ ፡ ነበር ። የመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ ያልሆኑ ፡ ሰዎችም ፡ መማር ፡ እንደሚፈልጉ ፡ ታየኝ ፤ ፍላጐታቸውም ፡ መርካት ፡ እንዳለበት ፡ ተገነዘብኩ ። የመጀመሪያው ፡ ዓመት ፡ ተማሪዎች ፡ አብዛኛዎቹ ፡ ጠበቆችና ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ ነበሩ ። ነገር ፡ ግን ፡ ሕግን ፡ ማወቅ ፡ ያለባቸው ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ ብቻ ፡ ሳይሆኑ ፡ ሌላው ፡ ሕዝብም ፡ ነው ።

አዲሱን ፡ ክፍል ፡ መክፈት ፡ ተፈላጊነት ፡ በደንብ ፡ ለማወቅ ፡ ፍላጐት ፡ ያላቸው ፡ ሰዎች ፡ በቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ የማታ ፡ ት/ቤት ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ መመዝገብ ፡ እንደሚችሉ ፡ የሚገልጽ ፡ ማስታወቂያ ፡ እንደገና ፡ በጋዜጦች ፡ ታተመ ። ፍላጐት ፡ ያላቸው ፡ በቂ ፡ ሰዎች ፡ ከተገኙ ፡ አዲስ ፡ ክፍል ፡ ለመክፈት ፡ ታቀደ ፤ ቢያንስ ፡ ከ፳፭—፴ ፡ ሰዎች ፡ እንዲመዘገቡ ፡ አስፈላጊ ፡ ነበር ። ብዛታቸው ፡ ከ፷ ፡ በላይ ፡ ሆኖ ፤ አብዛኞቹ ፡ የግል ፡ ሠራተኞች ፡ በተጨማሪም ፡ ከሰዓት ፡ በኋላ ፡ ፈቃድ ፡ ለማግኘት ፡ ያልቻሉ ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ ተመዘገቡ ። አዲስ ፡ ክፍል ፡ ለመጀመርና ፡ በተጨማሪም ፡ አስተማሪዎች ፡ ለመቅጠር ፡ ዝግጅት ፡ ተደረገ ። ጠቅላይ ፡ አቃቤ ፡ ሕጉ ፡ የተከበሩ ፡ አቶ ፡ አማኑኤል ፡ ዓምደ ፡ ሚካኤልና ፡ የተከበሩ ፡ አቶ ፡ ንጉሤ ፡ ፈታወቅ ፡ የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ፕሬዘዳንት ፡ አንዳንዶቹን ፡ ትምህርቶች ፡ ለማስተማር ፡ ተስማሙ ።

እኔ ፡ አስመራ ፡ ከደረስኩ ፡ ወዲህ ፡ በደምብ ፡ የተዘጋጀው ፡ አንዱ ፡ እቅዳችን ፤ በትምህርት ፡ ሚኒስትር ፡ ሕንጻ ፡ በሕዝብ ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ ውስጥ ፡ የሚ

ገኘው ፡ የሕግ ፡ ክፍል ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ እድገት ፡ ነው ። አዲስ ፡ አበባን ፡ በኅ ዳር ፡ ፲፱፻፶፯ ፡ ዓ. ም. በጐበኘሁበት ፡ ጊዜ ፡ አስመራው ፡ ት/ቤት ፡ የሚያገለግሉ ፡ ስለ ፡ ወንጀለኛ ፡ መቅጫና ፡ ስለ ፡ ወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ የተ ጻፉ ፡ መጻሕፍት ፡ እንዲገዙ ፡ ለዩኒቨርሲቲው ፡ የመጻሕፍቱን ፡ ዝርዝር ፡ አቀረ ብኩ ። እንደገና ፡ በመስከረም ፡ ፲፱፻፶፰ ፡ ዓ. ም. አዲስ ፡ አበባ ፡ በሄድኩበት ፡ ጊዜ ፡ ስለፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ስለ ፡ ዓለም ፡ አቀፍ ፡ ሕግ ፡ ስለ ፡ ሕግ ፡ ፍልስፍናና ፡ ጅሪስፕሩደንስ ፡ ስለ ፡ ታክስ ፡ ስለ ፡ ንብረት ፡ ሕግ ፡ ስለ ፡ አስተዳደር ፡ ሕግ ፡ ስለ ፡ የአውሮፓ ፡ ሕግ ፡ ታሪክ ፡ ወዘተ ፡ የሚገልጹ ፡ የመጻሕፍት ፡ ዝርዝር ፡ አዘጋጀሁ ። አሁን ፡ በቤተ ፡ መጻሕፍቱ ፡ ውስጥ ፡ ለሚገኙት ፡ መጻሕፍት ፡ መሟያ ፡ የሚሆኑ ፡ ፪፻፷ ፡ መጻሕፍት ፡ ደርሰውናል ። የመጻሕፍቶቹ ፡ አገዛዝ ፡ የተከናወነው ፡ ባዲስ ፡ አበባ ፡ የሕግ ፡ ፋኩልቲ ፡ ፕሮፌሰሮች ፡ አማካሪነትና ፡ በፍሮፌሰር ፡ ብሎስተይን ፡ የፋኩልቲው ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ አማካሪ ፡ እርዳታ ፡ ነው ።

ተማሪዎቹ ፡ በቤተ ፡ መጻሕፍቱ ፡ ውስጥ ፡ ባሉት ፡ መጻሕፍት ፡ እየተረዱ ፡ ማጥናት ፡ የክፍል ፡ መማሪያ ፡ ጽሑፋቸውን ፡ እንደሚያብራራላቸው ፡ ተገንዝበው ታል ። የትምህርት ፡ ሚኒስቴርም ፡ የራሳችንን ፡ ሕንጻ ፡ እስክናሰራ ፡ ድረስ ፡ ሕን ጻውን ፡ እንድንጠቀምበት ፡ ፈቅዶልናል ።

## ለ፲፱፻፶፱ ፡ ዓ.ም. ያለን ፡ ተስፋ ።

አሁን ፡ ለሕግ ፡ ምስክር ፡ ወረቀት ፡ የሚ ያጠኑ ፡ ሁለት ፡ ክፍሎች ፡ አሉን ። የሁለተኛው ፡ ዓመት ፡ የሕግ ፡ ምስክር ፡ ወረ ቀት ፡ ክፍል ፡ በሰኔ ፡ ፲፱፻፶፰ ፡ ዓ. ም. ይጨርሳል ፤ የምረቃው ፡ ሥነ ፡ ሥርዓትም ፡ በሰኔ ፡ ፳፭ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፱ ፡ ዓ. ም. ይከበራል ። ተማሪዎቹ ፡ የሕግ ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ፡ ይቀበላሉ ። ይህ ፡ የሁለተኛ ፡ ዓመት ፡ ክፍል ፡ ዲፕሎማ ፡ ወይም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ፡ የሚያስገኝ ፡ የንግድ ፡ ሕግ ፡ የማስረጃ ፡ ሕግና ፡ የውል ፡ ሕግን ፡ የያዘ ፡ ትምህርት ፡ በመካፈል ፡ ትምህርቱን ፡ ይቀጥላል ፡ ተብሎ ፡ ተስፋ ፡ ተጥሎበታል ።

የመጀመሪያ ፡ ዓመት ፡ ክፍል ፡ ተማሪዎች ፡ ሁለተኛ ፡ ዓመት ፡ ገብተው ፡ የሕገ ፡ መንግሥት ፡ ትምህርት ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓትንና ፡ የው ል ፡ ሕግ ፡ ይማራሉ ፤ በሐምሌ ፡ ወር ፡ ፲፱፻፶፱ ፡ ዓ. ም. ምስክር ፡ ወረቀት ፡ አግኝ ተው ፡ ይመረቃሉ ።

## በሕገ ፡ መንግሥት ፡ ትምህርት ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ፡ የሚያስገኝ ፡ ልዩ ፡ ፕሮግራም ።

በኅዳር ፡ ወር ፡ ፲፱፻፶፰ ፡ ዓ. ም. የፓርላማ ፡ ባልደረቦች ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ እናስተምራቸው ፡ ዘንድ ፡ ጠየቁን ። እንደተጠየቅነውም ፡ ፕሮ ግራሙን ፡ አዘጋጅተን ፡ ዩኒቨርሲቲው ፡ ተስማማበት ። የትምህርቱም ፡ ፕሮግራም ፡ የሕገ ፡ መንግሥት ፡ መሰረታዊ ፡ ሃሳብን ፡ የሕግ ፡ ማውጣት ፡ ሥነ ፡ ሥርዓትን ፡ የአስተዳደር ፡ ሕግንና ፡ የታክስ ፡ ሕግን ፡ የያዘ ፡ ነው ። በያዝነው ፡ ዓመት ፡ በያን ዳንዱ ፡ የትምህርት ፡ መንፈቅ ፡ ውስጥ ፡ ከ፴ ፡ ሰዓት ፡ በላይ ፡ አስተምረናቸዋል ። በየትምህርቱ ፡ መንፈቅ ፡ መጨረሻም ፡ ፈተና ፡ ተሰጥቷቸዋል ። ተማሪዎቹ ፡ ትም ህርታቸውን ፡ በአማርኛ ፡ ወይም ፡ በእንግሊዝኛ ፡ ለመከታተል ፡ ምርጫ ፡ ተሰጥ ቷቸው ፤ ፷ ፡ ለእንግሊዝኛው ፡ ክፍል ፡ ሲመዘገቡ ፡ ፴፮ ፡ ለአማርኛው ፡ ክፍል ፡ ተመ ዘገቡ ። እንደኔ ፡ አስተያየት ፡ ትምህርቱን ፡ በደንብ ፡ የተሳተፉት ፡ ይመስለኛል ፤ ምናልባትም ፡ ይህን ፡ የመሰሉ ፡ ፍላጐት ፡ ካለ ፡ አስፈላጊውን ፡ ትምህርት ፡ ለመ ስጠት ፡ እንችል ፡ ይሆናል ።

# የሕግ ፡ ተማሪዎች ፡ ቤት ፡ ውጥን ።

በፋኩልቲያችን ፡ ውስጥ ፡ የኤል ፡ ኤል ፡ ቢ ፡ ዲግሪ ፡ የሚያስገኘውን ፡ ትምህርት ፡ የሚከታተሉ ፡ ፫፻ ፡ የሙሉ ፡ ጊዜ ፡ ተማሪዎች ፡ አሉ ።

እነዚህ ፡ ተማሪዎች ፡ የመጡት ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛቶች ፡ ነው ። አብዛኞቹ ፡ ገንዘብ ፡ ያጥራቸዋል ፤ ከአዲስ ፡ አበባ ፡ ውጭ ፡ ከሚመጡትም ፡ የአብዛኞቹ ፡ መኖርያ ፡ ቤት ፡ ለተማሪ ፡ ኑሮ ፡ የሚስማማ ፡ አይደለም ።

የአብዛኞቹ ፡ ተማሪዎቻችን ፡ የኑሮ ፡ እኳኋን ፡ በጣም ፡ የሚያሳዝን ፡ ነው ። ዩኒቨርሲቲው ፡ የመኝታ ፡ ክፍል ፡ የለውም ። በዩኒቨርሲቲው ፡ አካባቢ ፡ የሚከራዩ ፡ ቤቶች ፡ ማግኘት ፡ በጣም ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው ። ለአብዛኞቹ ፡ ተማሪዎች ፡ ውሃና ኤሌክትሪክ ፡ ያላቸው ፡ ቤቶች ፡ ለመከራየት ፡ ከአቅማቸው ፡ በላይ ፡ ነው ።

ይህ ፡ ሁናቴ ፡ ለተማሪዎቹ ፡ ጤናና ፡ ሞራል ፡ መጥፎ ፡ ከመሆኑም ፡ በላይ ፡ የትምህርት ፡ ደረጃቸውን ፡ ዝቅ ፡ ያደርገዋል ። ይህ ፡ ሁናቴ ፡ መታረም ፡ አለበት ፤ ምክንያቱም ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ የብዙ ፡ ሰዓታት ፡ ጥልቅ ፡ ንባብ ፡ ስለሚጠይቅ ፡ ነው ። በተጨማሪም ፡ ተማሪዎቹ ፡ እርስ ፡ በራሳቸው ፡ እንዲከራከሩና ፡ እንዲግባቡ ፡ ያስፈልጋል ። የሕግ ፡ ትምህርት ፡ መጀመር ፡ በሞያ ፡ ሥራ ፤ መሰማራት ፡ ማለት ፡ ነው ።

በአስተማሪዎች ፡ አማካሪነት ፡ ተማሪዎቹ ፡ ራሳቸውን ፡ በጣም ፡ ለተቸገሩት ፡ ተማሪዎች ፡ መኖሪያ ፡ ቤት ፡ ለማስገኘት ፡ በመጣጣር ፡ ላይ ፡ ናቸው ።

ተማሪዎቹ ፡ "የሕግ ፡ ተማሪዎች ፡ ቤት" ፡ ለማሠራት ፡ በሕግ ፡ ተማሪዎች ፡ ማኅበር ፡ የሚተዳደር ፤ ራሥን ፡ በራስ ፡ የመርዳት ፡ ፕሮግራም ፡ አዘጋጅተዋል ።

"የሕግ ፡ ተማሪዎች ፡ ቤት ፡" በየክፍሉ ፡ ሁለት ፡ ልጆች ፡ በጠቅላላው ፡ ፵ ፡ ልጆች ፡ ይይዛል ፤ መጠነኛ ፡ የመዝናኛ ፡ ቦታና ፡ የመታጠቢያ ፡ ክፍል ፡ ይኖረዋል። በተጨማሪም ፡ የቀድሞ ፡ የሕግ ፡ ተማሪዎችና ፡ የሕግ ፡ ተማሪዎች ፡ በየጊዜው ፡ የሚገናኙበት ፡ ቦታ ፡ ይሆናል ።

ዩኒቨርሲቲው ፡ ለቤቱ ፡ ማሠሪያ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ መሬት ፡ ሰጥቷል ። የሕንጻውን ፡ ማሠራትና ፡ ማካሄዱ ፡ ኃላፊነት ፡ የሕግ ፡ ተማሪዎች ፡ ማኅበር ፡ ይወስዳል። ማኅበሩም ፡ ሕንጻውን ፡ ለማሠራት ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ውስጥ ፡ ከሚገኘው ፡ የሕግ ፡ "ኰሚ" ፡ እና ፡ ከሌላ ፡ ቦታም ፡ እርዳታ ፡ ይፈልጋል ። እርግጠኛ ፡ ባንሆንም ፤ ሕዝቡ ፡ ቢረዳ ፡ ዓላማችን ፡ ከግብ ፡ እንደሚደርስልን ፡ ተስፋ ፡ እናደርጋለን ።

ይህ ፡ ፕሮግራም ፡ የዓርአያነት ፡ ፕሮግራም ፡ ነው ። የዚህ ፡ ዓይነት ፡ ፕሮግራም ፡ በዩኒቨርሲቲው ፡ ውስጥ ፡ ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ መሞከሩ ፡ ነው ። የሕግ ፡ ተማሪዎችን ፡ ፍላጐት ፡ ከማርካት ፡ ሌላ ፤ ይህ ፡ ፕሮግራም ፡ ተማሪዎችና ፡ አስተማሪዎች ፡ በመተባበር ፡ እንዴት ፡ አድርገው ፡ የዩኒቨርሲቲውን ፡ የቤት ፡ ማነስ ፡ ችግር፡ እንደሚያስወግዱ ፡ ያስተምራል ፡ ብለን ፡ እናምንበታለን ።

በመጨረሻም ፡ ተስፋ ፡ የማደርገው ፡ "የሕግ ፡ ተማሪዎች ፡ ቤት" ፡ የሕጉን ፡ ት/ቤት ፡ የመጀመሪያ ፡ ትውልድ ፡ ዓላማ ፡ ብሱልነትና ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ ያሳያል ፡ እያልኩ ፡ ነው ። ይህ ፡ ተግባር ፡ ለወደፊት ፡ የሕግ ፡ ተማሪዎችም ፡ የተቀደሰ ፡ የኩራት ፡ መንፈስ ፡ ያሳድርባቸዋል ፡ ብዬ ፡ ተስፋ ፡ አደርጋለሁ ። አስፈላጊው ፡ እርዳታ ፡ ተገኝቶ ፡ ውጥኑ ፡ እግቡ ፡ እንደሚደርስም ፡ ተስፋ ፡ አደርጋለሁ ።

## በሕግ ፡ ፋኩልቲ ፡ ተማሪዎች ፡ የ፲፱፻፶፯-፲፱፻፶፰ ፡ ዓ.ም. ።

### በሕግ ፡ የኤል. ኤል. ቢ. ዲግሪ ፡ በሰኔ ፡ ወር ፡ ፲፱፻፶፰ ፡ ዓ.ም. አግኝተው ፡ የተመረቁ ፡

### የሙሉ ፡ ቀን ፡ ተማሪዎች ።

ሚስ ፡ አሌክሳንደራ ፡ ሐማዊ ፡
የመቶ ፡ አለቃ ፡ ማሞ ፡ መዘምር ፡
አቶ ፡ ሥሑል ፡ ሚካኤል ፡
አቶ ፡ ሰላሙ ፡ በቀለ ፡
አቶ ፡ ሽመልስ ፡ ሑሴን ፡
አቶ ፡ ኃይሉ ፡ ሚካኤል ፡ ከበደ ፡
የመቶ ፡ አለቃ ፡ አበራ ፡ ባንቲዋሉ ፡
የሻምበል ፡ አበበ ፡ ጓንጉል ፡
አቶ ፡ አባቢያ ፡ አባጆቢር ፡
የመቶ ፡ አለቃ ፡ ኢያሱ ፡ አያል ፡
አቶ ፡ ዘርዓ ፡ ብሩክ ፡ አበራ ፡
አቶ ፡ ያዕቆብ ፡ ኃይሉ ፡ ማርያም ፡
አቶ ፡ ዮሐንስ ፡ ጎሩይ ፡
የመቶ ፡ አለቃ ፡ ዳንኤል ፡ ዘለቀ ፡
አቶ ፡ ገብረ ፡ ሕይወት ፡ አረጋይ ፡
የመቶ ፡ አለቃ ፡ ጌታሁን ፡ ዳምጤ ፡
አቶ ፡ ግርማ ፡ ታደሰ ።

### በሕግ ፡ የኤል. ኤል ቢ. ዲግሪ ፡ በሰኔ ፡ ወር ፡ ፲፱፻፶፱ ፡ ዓ. ም. አግኝተው ፡

### የሚመረቁ ፡ የግማሽ ፡ ቀን ፡ (የማታ ፡ ተማሪዎች) ።

አቶ ፡ መብራህቱ ፡ ዮሐንስ ፡
አቶ ፡ መንገሻ ፡ ወርቅነህ ፡
አቶ ፡ ሰይፉ ፡ ፈለቀ ፡
አቶ ፡ ቡልቻ ፡ ደመቅሣ ፡
አቶ ፡ ነቢይ ፡ ልዑል ፡ ክፍሌ ፡
አቶ ፡ ነጋ ፡ ፋንታ ፡
አቶ ፡ አሰፋ ፡ ጸጋዬ ፡
ክቡር ፡ አቶ ፡ አበራ ፡ ጀምበሬ ፡
አቶ ፡ እጅጉ ፡ ደምሴ ፡
አቶ ፡ ከበደ ፡ ገብረ ፡ ማርያም ፡
አቶ ፡ ካሣ ፡ በየነ ፡ አየለ ፡
አቶ ፡ ወርቁ ፡ ተፈራ ፡
አቶ ፡ ዓቢዮ ፡ ገለታ ።

### በሕግ ፡ የኤል. ኤል. ቢ. ዲግሪ ፡ በሰኔ ፡ ወር ፡ ፲፱፻፶፱ ፡ ዓ. ም. አግኝተው ፡

### የሚመረቁ ፡ የሙሉ ፡ ቀን ፡ ተማሪዎች ።

የሻምበል ፡ መስፍን ፡ ገብረ ፡ ቃል ፡
አቶ ፡ ሠመረ ፡ አብ ፡ ሚካኤል ፡
የመቶ ፡ አለቃ ፡ ሽመልስ ፡ መታፈሪያ ፡
አቶ ፡ በቀለ ፡ ወልዴ ፡
የመቶ ፡ አለቃ ፡ ብርሃኑ ፡ ባይህ ፡
አቶ ፡ ተክሉ ፡ መኮንን ፡
አቶ ፡ ታዬ ፡ ንጋቱ ፡
የሻምበል ፡ ታደሰ ፡ አብዲ ፡
አቶ ፡ ታደሰ ፡ ጉርሙ ፡
የመቶ ፡ አለቃ ፡ ኃይሉ ፡ መኮንን ፡
አቶ ፡ አበበ ፡ ወርቄ ፡
አቶ ፡ ክሰተ ፡ ኃይሌ ፡
አቶ ፡ ከበደ ፡ ካሣ ፡
የመቶ ፡ አለቃ ፡ ወንዳየን ፡ ምሕረቱ ፡
አቶ ፡ ዓለሙ ፡ ደነቀው ፡
የመቶ ፡ አለቃ ፡ ዓለማየሁ ፡ አስፋው ፡
አቶ ፡ ዘመኑ ፡ ካሰኝ ፡
የመቶ፡አለቃ ፡ ዘርአይ ፡ ሀብተ፡ሥላሴ፡
አቶ ፡ ዘገየ ፡ አስፋው ፡
የመቶ ፡ አለቃ ፡ ይልማ ፡ ግዛው ፡
አቶ ፡ ጣዓመ ፡ በየነ ፡
አቶ ፡ ጥዑመልሳን ፡ ለማ ፡
አቶ ፡ ፋሲል ፡ ናሆም ፡
አቶ ፡ ፍሥሐ ፡ ባይህ ።

## በሕግ ፡ የኤል ፡ ኤል ፡ ቢ ፡ ዲግሪ ፡ በሰኔ ፡ ወር ፡ ፲፱፻፳ ፡ ዓ ፡ ም ፡ አግኝተው ፡ የሚመረቁ ፡ የሙሉ ፡ ቀን ፡ ተማሪዎች ።

መቶ ፡ አለቃ ፡ ለማ ፡ ጉተማ ፡
አቶ ፡ ላቀው ፡ ብርሃኔ ፡
አቶ ፡ ሰይፉ ፡ ተክለማርያም ፡
አቶ ፡ ቢልልኝ ፡ ማንደፍሮ ፡
አቶ ፡ ተሰፋ ፡ አያና ፡
አቶ ፡ ተስፋዬ ፡ ጨምር ፡
አቶ ፡ ተድላ ፡ ጉተማ ፡
መቶ ፡ አለቃ ፡ ታጠቅ ፡ ታደሰ ፡
አቶ ፡ አለማንቴ ፡ ገብረሥላሴ ፡
አቶ ፡ ዓለማየሁ ፡ ሰይፉ ፡
አቶ ፡ አለምሰገድ ፡ ተሰፋዬ ፡
አቶ ፡ አምሐጽዮን ፡ ዶመኒክ ፡
አቶ ፡ አሸብር ፡ ተፈራ ፡
አቶ ፡ አበራ ፡ ደጉ ፡
አቶ ፡ ኢሳያስ ፡ ኃይለ ፡ ማርያም ፡
አቶ ፡ ኢያሱ ፡ እምነቱ ፡
አቶ ፡ ኤደን ፡ ፋሲል ፡
አቶ ፡ ከበደ ፡ ክፍሌ ፡
አቶ ፡ ይልማ ፡ ኃይሉ ፡
አቶ ፡ ዮሴፍ ፡ ገብረ ፡ እግዚአብሔር ፡
መቶ ፡ አለቃ ፡ ዮሴፍ ፡ ያዘው ፡
አቶ ፡ ዮሐንስ ፡ ሀብተሥላሴ ፡
ሚስተር ፡ ጆርጅ ፡ ካንዳዋሬ ፡
አቶ ፡ ገብሩ ፡ መርሻ ፡
አቶ ፡ ገድለ ፡ አማኑኤል ፡ ኪዳነማርያም ፡
አቶ ፡ ጊድዎን ፡ አገኘ ፡
መቶ ፡ አለቃ ፡ ጌታቸው ፡ አበበ ፡
ሻለቃ ፡ ጌታቸው ፡ ኃይሌ ፡
አቶ ፡ ጌታሁን ፡ መታፈሪያ ፡
አቶ ፡ ግርማ ፡ ሥላሴ ፡ አርአያ ።

## በሕግ ፡ ዲፕሎማ ፡ በሰኔ ፡ ወር ፡ ፲፱፻፶፱ ፡ ዓ.ም. አግኝተው ፡ የሚመረቁ ፡ ተማሪዎች።

አቶ ፡ መስፍን ፡ አምባቸው ፡
አቶ ፡ መስፍን ፡ ፋንታ ፡
አቶ ፡ መንክር ፡ ገብረ ፡ ማርያም ፡
አቶ ፡ ሙላቱ ፡ ልካሳ ፡
አቶ ፡ ምናሴ ፡ ደጉ ፡
አቶ ፡ ሠይፉ ፡ ፈይሣ ፡
አቶ ፡ ሰይፉ ፡ አናጌ ፡
አቶ ፡ ሰይፉ ፡ የተሻ ፡ ወርቅ ፡
አቶ ፡ ሳሙኤል ፡ ወርቅነህ ፡
ሚስተር ፡ አራኪል ፡ ሳካጂያን ፡
አቶ ፡ በቀለ ፡ ተስፋዬ ፡
አቶ ፡ ብርሃኑ ፡ ሣህለ ፡ ጊዮርጊስ ፡
አቶ ፡ ብርሃኑ ፡ ክፈተው ፡
አቶ ፡ ተስፋዬ ፡ ሣህሌ ፡
አቶ ፡ ተስፋዬ ፡ ዓለሙ ፡
የመቶ ፡ አለቃ ፡ ተሾመ ፡ በየነ ፡
አቶ ፡ ተሾመ ፡ ገ/ሥላሴ ፡
የሻምበል ፡ ታምሩ ፡ ኃይለ ፡ ገብርኤል ፡
የሻምበል ፡ ታዬ ፡ ወልዴ ፡ ጊዮርጊስ ፡
አቶ ፡ ወንድማገኘሁ ፡
አቶ ፡ ኃይሉ ፡ ወልደሚካኤል ፡
አቶ ፡ ኃይሉ ፡ ወልዴ ፡ ማርያም ፡
የመቶ ፡ አለቃ ፡ ነጋሽ ፡ ተክለ ፡ ማርያም ፡
አቶ ፡ አሰፋ ፡ በቀለ ፡
የመቶ ፡ አለቃ ፡ አሰፋ ፡ ኃይለ ፡ ማርያም ፡
የመቶ ፡ አለቃ ፡ አበራ ፡ ጐበና ፡
አቶ ፡ አብርሃም ፡ ጸጋዬ ፡
ሚስስ ፡ ማሪክ ፡ አርጓኒቶፖ ፡
አቶ ፡ አክሊሉ ፡ አጥላባቸው ፡
አቶ ፡ አክሊሉ ፡ ቤተ ፡ ማርያም ፡
የመቶ ፡ አለቃ ፡ እርዳው ፡ ዳርጌ ፡
የሻምበል ፡ ካሣዬ ፡ ማንደፍሮህ ፡
አቶ ፡ ካሣዬ ፡ አደም ፡
አቶ ፡ ክፈለኝ ፡ ማንያዘዋል ፡
የሻምበል ፡ ወልዴ ፡ ሐዋርያት ፡ ገ/ማርያም ፡
ሻሽራሻ ፡ ዘውዴ ፡ አቶሮ ፡
የሻለቃ ፡ ይልማ ፡ ወልደሰማያት ፡
አቶ ፡ ደምሴ ፡ በቀለ ፡
አቶ ፡ ጀማነህ ፡ መካሻ ፡
ሚስተር ፡ ጆዋኪም ፡ ማቶቹ ፡
አቶ ፡ ጆሴፍ ፡ ኃይሌ ፡
አቶ ፡ ገብረየሱስ ፡ ኃይለማርያም ፡
አቶ ፡ ጉደታ ፡ ቦሩ ፡
የሻምበል ፡ ጌታሁን ፡ በቀለ ፡
አቶ ፡ ግርማይ ፡ ዘወልዴ ፡
አቶ ፡ ጸደቀ ፡ ተክሌ ።

## በሕግ ፡ ዲፕሎማ ፡ በሰኔ ፡ ወር ፡ ፲፱፻፷ ፡ ዓ ፡ ም ፡ አግኝተው ፡ የሚመረቁ ፡ ተማሪዎች ፡ (የእንግሊዝኛ ፡ ክፍል) ።

መቶ ፡ አለቃ ፡ ሙሉ ፡ ዋሴ ፡
አቶ ፡ ሰሎሞን ፡ አበበ ፡
አቶ ፡ ሸዋቀና ፡ ዜና ፡
አቶ ፡ በላቸው ፡ ዘመድኩን ፡
አቶ ፡ ብርሃኑ ፡ ኪዳኔ ፡
አቶ ፡ ተሰማ ፡ ገብረሥላሴ ፡
አቶ ፡ ታመነ ፡ ጥላዬ ፡
አቶ ፡ ታደሰ ፡ ታየ ፡
አቶ ፡ ታደሰ ፡ ቤተማርያም ፡
አቶ ፡ ታደሰ ፡ ቦጋለ ፡
አቶ ፡ ኃይሌ ፡ አምላክ ፡ ኃይለ ፡ መለኮት ፡
ሻለቃ ፡ ንጉሤ ፡ ወልደ ፡ ሚካኤል ፡
አቶ ፡ ዓለሙ ፡ ረዘነ ፡
አቶ ፡ አለም ፡ ሰገድ ፡ ገ/እግዚአብሔር ፡
አቶ ፡ አረአያ ፡ መድህን ፡ መርሻ ፡
አቶ ፡ አስናቀ ፡ ታደሰ ፡
መቶ ፡ አለቃ ፡ አሰፋ ፡ ኃይሌ ፡
አቶ ፡ አባተ ፡ ወንድምአገኘሁ ፡
ቄስ ፡ ኤርምያስ ፡ ከበደ ፡
አቶ ፡ እሸቴ ፡ ተሰማ ፡
መቶ ፡ አለቃ ፡ እንግዳ ፡ ወልደ ፡ አምላክ ፡
አቶ ፡ ከሰተ ፡ በራኪ ፡
አቶ ፡ ከበደ ፡ ዮሴፍ ፡ በርቶሎሚዩስ ፡
አቶ ፡ ኩምሳ ፡ ለታ ፡
መቶ ፡ አለቃ ፡ ካሣሁን ፡ ቢራቱ ፡
መቶ ፡ አለቃ ፡ ወንድይፍራው ፡ በለው ፡
መቶ ፡ አለቃ ፡ ደበበ ፡ ኃይሉ ፡
አቶ ፡ ጌታቸው ፡ ተምትሜ ፡
አቶ ፡ ግርማ ፡ መንግሥቱ ፡
ሻምበል ፡ ግርማ ፡ ዘውዴ ፡
መቶ ፡ አለቃ ፡ ጥላሁን ፡ ትርፌ ።

## በሕግ ፡ ዲፕሎማ ፡ በሰኔ ፡ ወር ፡ ፲፱፻፶፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ አግኝተው ፡ የሚመረቁ ፡ ተማሪዎች ፡ (የአማርኛ ፡ ክፍል) ።

አቶ ፡ ለማ ፡ ትርፌ ፡
ፊታ/ሎልበጂ ፡ ሰዩም ፡
አቶ ፡ መኮንን ፡ አንኖናፍር ፡
አቶ ፡ መኮንን ፡ ደስታ ፡
አቶ ፡ መኮንን ፡ ወልደ ፡ ማርያም ፡
መዘምር ፡ መልከጸድቅ ፡ ወልደ ፡ ሥላሴ ፡
አቶ ፡ ሙሉጌታ ፡ ኃብተ ፡ ገብርኤል ፡
አቶ ፡ ሙሉጌታ ፡ በሪሁን ፡
አቶ ፡ ሙሉጌታ ፡ አካሉ ፡
አቶ ፡ ሙሉጌታ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስ ፡
ሻለቃ ፡ ሙላት ፡ እንዳይላሉ ፡
ሻምበል ፡ ሰሙን ፡ ንዋይ ፡
አቶ ፡ ሱልጣን ፡ ሰይድ ፡
አቶ ፡ ሸዋዬ ፡ ለማ ፡
አቶ ፡ ሸዋንግዛው ፡ ወልደ ፡ ዮሐንስ ፡
አቶ ፡ ሽመልስ ፡ ተፈራ ፡
አቶ ፡ በለጠ ፡ በረደድ ፡
ወይዘሮ ፡ በልዩ ፡ ገብረ ፡ መስቀል ፡
አቶ ፡ በላቸው ፡ ገዝሙ ፡
አቶ ፡ በላይ ፡ መንገሻ ፡
አቶ ፡ በርሄ ፡ ፀጋዬ ፡
መቶ ፡ አለቃ ፡ በየነ ፡ ባልቻ ፡
አቶ ፡ ብርሃኑ ፡ ከበደ ፡
ኰሎኔል ፡ ብርሃኑ ፡ ወልደየስ ፡
ሻምበል ፡ ተስፋዬ ፡ መንገሻ ፡
ሻለቃ ፡ ተስፋዬ ፡ ገብረየስ ፡
አቶ ፡ ተረፈ ፡ ገሠሠ ፡
አለቃ ፡ ተክለተ ፡ ብርሃን ፡ ወልደየሱስ ፡
አቶ ፡ ተወልደ ፡ አብረሃ ፡
አቶ ፡ ታምሩ ፡ ገብረ ፡ መድኅን ፡
አቶ ፡ ታደሰ ፡ አከሎግ ፡
ሻምበል ፡ ታደሰ ፡ እንግዳ ፡
አቶ ፡ ታደሰ ፡ ካሣዬ ፡
መቶ ፡ አለቃ ፡ ታደሰ ፡ ገመዳ ፡
አቶ ፡ ታዬ ፡ ተፈራ ፡
አቶ ፡ ንጉሤ ፡ ነውጤ ፡
አቶ ፡ ንጉሤ ፡ አበበ ፡
ሻለቃ ፡ ዓለሙ ፡ ግዛው ፡
አቶ ፡ ዓለሙ ፡ መለሰ ፡
አቶ ፡ ዓለማየሁ ፡ በላይ ፡
አቶ ፡ ዓለማየሁ ፡ ቦጋለ ፡
አቶ ፡ ዓለማየሁ ፡ ገብረ ፡ ተክሉ ፡

አቶ ፡ ዓለማየሁ ፡ ጉልላት ፡
ቀኝ ፡ ጌታ ፡ አለባቸው ፡ ካሣ ፡
አቶ ፡ አመዴ ፡ ለማ ፡
አቶ ፡ አማረ ፡ ሙላት ፡
መቶ ፡ አለቃ ፡ አስፋ ፡ መንገሻ ፡
አቶ ፡ አስፋ ፡ ወሰን ፡
አቶ ፡ አስገደው ፡ አመነሸዋ ፡
አቶ ፡ አበበ ፡ ጅሬ ፡
አቶ ፡ አባሆይ ፡ አረፈዓይኔ ፡
መቶ ፡ አለቃ ፡ አጥላባቸው ፡
አቶ ፡ አያሌው ፡ አየነ ፡
አቶ ፡ እሙን ፡ ተመልሶ ፡
አቶ ፡ እሸቱ ፡ ደምሴ ፡
አቶ ፡ እናለ ፡ ዘወልዴ ፡
አቶ ፡ ከበደ ፡ ኃብተ ፡ ማርያም ፡
ሻምበል ፡ ከበደ ፡ በቀለ ፡
መቶ ፡ አለቃ ፡ ክፍሌ ፡ በላይ ፡
መቶ ፡ አለቃ ፡ ከተማ ፡ ደስታ ፡

አቶ ፡ ወልደ ፡ ሚካኤል ፡ ገብረአብ ፡
አቶ ፡ ይልማ ፡ ታደሰ ፡
መቶ ፡ አለቃ ፡ ይልማ ፡ መንግሥቱ ፡
አቶ ፡ ደምሴ ፡ ያደቴ ፡
አቶ ፡ ደርባቸው ፡ ሞሐመድ ፡
መቶ ፡ አለቃ ፡ ደበበ ፡ ካሣ ፡
አቶ ፡ ገብረሕይወት ፡ ወልደ ፡ ሐዋርያት ፡
አቶ ፡ ገብረ ፡ ማርያም ፡ መርጊያ ፡
አቶ ፡ ገዛኸኝ ፡ ወልዱ ፡
አቶ ፡ ጋረደው ፡ በላይነህ ፡
አቶ ፡ ጌታቸው ፡ አስፋው ፡
መቶ ፡ አለቃ ፡ ጌታቸው ፡ ውብነህ ፡
አቶ ፡ ጌታቸው ፡ ምንልኬ ፡
አቶ ፡ ጌታነህ ፡ ውብነህ ፡
አቶ ፡ ጐሳዬ ፡ ዘመድኩን ፡
አቶ ፡ ጐይቶም ፡ በየነ ፡
አቶ ፡ ጥበቡ ፡ አብርሃም ፡
መቶ ፡ አለቃ ፡ ፈቃዱ ፡ ዋኬዐ ።

<u>በሕግ፡ ሠርቲፊኬት፡ በሰኔ፡ ወር፡ ፲፱፻፶፰፡ ዓ. ም. አግኝተው፡ የተመረቁ፡ ተማሪዎች።</u>

<u>(አዲስ ፡ አበባ ፡ ክፍል «ሀ») ።</u>

አቶ ፡ ለማ ፡ ደገፉ ፡
ሌ/ኰ ፡ መርድ ፡ አስፋው ፡
አቶ ፡ መቆያ ፡ እሼቴ ፡
አቶ ፡ መኰንን ፡ አስፋው ፡
አቶ ፡ ሙሉጌታ ፡ ይመኑ ፡
አቶ ፡ ምስጋና ፡ ታረቀኝ ፡
መምሬ ፡ ሚህለድንግል ፡ ገብረክርስቶስ ፡
አቶ ፡ ሰሎሞን ፡ ዳኛቸው ፡
የመቶ ፡ አለቃ ፡ ሰብስቤ ፡ ከበደ ፡
አቶ ፡ ሰዋስው ፡ እንየው ፡
አቶ ፡ ስለሺ ፡ ደስታ ፡
አቶ ፡ በላይ ፡ ጌታሁን ፡
አቶ ፡ በቀለ ፡ ወልደዮሐንስ ፡
አቶ ፡ ተስፋዬ ፡ በዛብህ ፡
አቶ ፡ ተሾመ ፡ ገላግል ፡
አቶ ፡ ተካ ፡ ገብረ ፡ ሕይወት ፡
አቶ ፡ ተፈራ ፡ በየነ ፡
የሻለቃ ፡ ታምራት ፡ ጐበዜ ፡
አቶ ፡ ታደሰ ፡ አብተው ፡
አቶ ፡ ታደሰ ፡ ወልደኪዳን ፡
አቶ ፡ ቴዎድሮስ ፡ አረፈ ፡ ዓይኔ ፡
አቶ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ሐጐስ ፡

አቶ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ በዛብህ ፡
የሻምበል ፡ ኃይሉ ፡ ደስታ ፡
አቶ ፡ ኃይሌ ፡ ወልደ ፡ ሐና ፡
አቶ ፡ ንጋቱ ፡ ሀብተማርያም ፡
የሻምበል ፡ አማረ ፡ አዱራ ፡
አቶ ፡ አሰፋ ፡ ተገኝ ፡
አቶ ፡ አሰፋ ፡ አካለ ፡ ሕይወት ፡
አቶ ፡ አሰፋ ፡ አየለ ፡
አቶ ፡ አስፋው ፡ ይትባረክ ፡
አቶ ፡ አስቤ ፡ ገብረ ፡ ሥላሴ ፡
አቶ ፡ አሻግሬ ፡ ኃይሉ ፡
አቶ ፡ አበበ ፡ አውግቸው ፡
አቶ ፡ አብርሃም ፡ ተክሌ ፡
አቶ ፡ አብርሃም ፡ ድሬሳ ፡
አቶ ፡ አንዱ ፡ ዓለም ፡ በላይ ፡
አቶ ፡ አየለ ፡ ወልደ ሐዋርያት ፡
አቶ ፡ አያሌው ፡ ደስታ ፡
አቶ ፡ እሼቴ ፡ ገብረ ፡ ማርያም ፡
አቶ ፡ እንዳለው ፡ መንገሻ ፡
አቶ ፡ እንግዳ ፡ ጌጥ ፡ ወርቁ ፡
የሻምበል ፡ ከበደ ፡ ሰንበቶ ፡
አቶ ፡ ካሣሁን ፡ አበበ ፡

አቶ ፡ ወርቁ ፡ ወልዴ ፡ አረጋይ ፡
የሻለቃ ፡ ወንድሙ ፡ ገብረ ፡ ማርያም ፡
አቶ ፡ ውቤ ፡ ወልደየስ ፡
የሻለቃ ፡ ዘሪሁን ፡ ገብረሥላሴ ፡
አቶ ፡ ዘውዴ ፡ መዝገቡ ፡
አቶ ፡ ዘውዴ ፡ ተድላ ፡
አቶ ፡ የማነብርሃን ፡ ወንድምአየሁ ፡
የሻለቃ ፡ የኔነህ ፡ ዓለሙ ፡
አቶ ፡ ደሳለኝ ፡ ዓለሙ ፡
ሌ/ኰ ደባልቄ ፡ ገዳ ፡
አቶ ፡ ጥላሁን ፡ ኃይሌ ፡
አቶ ፡ ጥላሁን ፡ አስፋው ፡
አቶ ፡ ጽጌ ፡ ደርሰህ ፡
አቶ ፡ ፈለቀ ፡ ደምሴ ፡
አቶ ፡ ፍሬ ፡ ሕይወት ፡ በይበይን ፡

<u>በሕግ፡ሠርቲፊኬት፡በሰኔ፡ወር፡፲፱፻፶፰፡ዓ.ም. ያገኙት አማኙተው፡የተመረቁ፡ተማሪዎች።</u>

(አዲስ ፡ አበባ ፡ ክፍል ፡ «ለ»)

አቶ ፡ ለማ ፡ ተረፈ ፡
ሌ/ኰ ሉልሰገድ ፡ ኃይሌ ፡
የመቶ ፡ አለቃ ፡ ሉልሰገድ ፡ ንጉሤ ፡
የሻምበል ፡ መለስ ፡ መቼሳ ፡
የመቶ ፡ አለቃ ፡ መለሰ ፡ ዓለሙ ፡
ሐጂ ፡ መሐመድ ፡ ሲራጅ ፡
አቶ ፡ መስፍን ፡ ማሞ ፡
አቶ ፡ መስፍን ፡ ተፈራ ፡
አቶ ፡ መርጋ ፡ ሰኝ ፡
የመቶ ፡ አለቃ ፡ መንገሻ ፡ ዘውዴ ፡
የመቶ ፡ አለቃ ፡ መንግሥቱ ፡ በጋሻው ፡
አቶ ፡ ሙሉጌታ ፡ እንዳለ ፡
አቶ ፡ ማሙዬ ፡ መሸሻ ፡
አቶ ፡ ማሞ ፡ ወልደማርያም ፡
የአሥር ፡ አለቃ ፡ ምንይል ፡ ሸዋ ፡ ሀብቴ ፡
አቶ ፡ ሞሲሳ ፡ ጋሪ ፡
አቶ ፡ ሰይፉ ፡ ቢጂያ ፡
አቶ ፡ ሥዩም ፡ ኃይለሚካኤል ፡
አቶ ፡ ሥዩም ፡ አበበ ፡
አቶ ፡ ሣህሉ ፡ ምሕረቱ ፡
አቶ ፡ ሽፈራው ፡ መሸሻ ፡
አቶ ፡ በቀለ ፡ ደምሴ ፡
አቶ ፡ ብርሃኑ ፡ አባይ ፡
አቶ ፡ ብርቁ ፡ አባሡራን ፡
አቶ ፡ ተስፋዬ ፡ ዱባለ ፡
አቶ ፡ ተረፈ ፡ ገብረመስቀል ፡
አቶ ፡ ተሾመ ፡ ቢረሳው ፡
አቶ ፡ ተከስተ ፡ ብርሃን ፡ ድባቡ ፡
ኰሎኔል ፡ ተክለማርያም ፡ አባይሬ ፡
አቶ ፡ ተክሌ ፡ ገብረ ፡ መስቀል ፡
አቶ ፡ ተገኝ ፡ ሀብቴ ፡
አቶ ፡ ተገኝ ፡ ወንዳፍራሽ ፡
የመቶ ፡ አለቃ ፡ ታየ ፡ ቁምላቸው ፡
የሻምበል ፡ ታደሰ ፡ ተስፋ ፡
አቶ ፡ ታደሰ ፡ አበበ ፡
አቶ ፡ ታደሰ ፡ ወልደጻድቅ ፡
አቶ ፡ ታደሰ ፡ ጭጭ ፡ አይበሉ ፡
ያምሳ ፡ አለቃ ፡ ታደሰ ፡ ፈይሳ ፡
አቶ ፡ ኃይለ ፡ ልዑል ፡ ሀብተዮሐንስ ፡
አቶ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ አስፋው ፡
አቶ ፡ ኃይለ ፡ ኢየሱስ ፡ ሙላት ፡
አቶ ፡ ኃይሌ ፡ አጕናፍር ፡
ሌ/ኰ አህመድ ፡ አሚኑ ፡
አቶ ፡ አለነ ፡ ወንዴ ፡
የሻምበል ፡ አማረ ፡ ንጋቱ ፡
አቶ ፡ አማረ ፡ ደግፌ ፡
አቶ ፡ አራጋው ፡ ወልዴ ፡
አቶ ፡ አሰፋ ፡ ዘአማኑኤል ፡
አቶ ፡ አሰፋ ፡ ደስታ ፡
አቶ ፡ አስፋው ፡ መሸሻ ፡
አቶ ፡ አስፋው ፡ ገብረኢየሱስ ፡
አቶ ፡ አበበ ፡ ተሰማ ፡
አቶ ፡ አበበ ፡ አስገልጥ ፡
አቶ ፡ አድማሱ ፡ አስረስ ፡
የሻለቃ ፡ አድማሱ ፡ ጀምበሬ ፡
አቶ ፡ አድማሴ ፡ ገሠሠ ፡
ወይዘሮ ፡ ዓይኔ ፡ አበባ ፡ ሸዋንግዥው ፡
አቶ ፡ እጋ ፡ ነጋሽ ፡
አቶ ፡ እሸቱ ፡ ከበደ ፡
አቶ ፡ ከበደ ፡ ተረፈ ፡
መቶ ፡ አለቃ ፡ ከፋለ ፡ አድገህ ፡
አቶ ፡ ካሳሁን ፡ ወርቅነህ ፡
አቶ ፡ ወልደትንሣኤ ፡ ገብረሚካኤል ፡
አቶ ፡ ወልደጻድቅ ፡ ወልደሰማዕት ፡

አቶ ፡ ወንድሙ ፡ ገብረመድኅን ፡
አቶ ፡ ወንድወሰን ፡ በቀለ ፡
አቶ ፡ ዓለማየሁ ፡ አጋ ፡
አቶ ፡ ዓለማየሁ ፡ ወንድሙ ፡
አቶ ፡ ዓለምሰገድ ፡ አርአያ ፡
አቶ ፡ ዕጹብ ፡ ደስታ ፡
አቶ ፡ የማነ ፡ ብርሃን ፡ መላኩ ፡
አቶ ፡ ይልማ ፡ በቀለ ፡
አቶ ፡ ይትባረክ ፡ ተሾመ ፡
አቶ ፡ ዲሚጥሮስ ፡ ገብረሐና ፡
አቶ ፡ ዳባ ፡ ሱንጣ ፡
አቶ ፡ ገላሁን ፡ አባተ ፡
አቶ ፡ ገመቹ ፡ ጉታ ፡
አቶ ፡ ገብረሥላሴ ፡ ደስታ ፡
አቶ ፡ ፋንታሁን ፡ ብርሃኑ ፡
አቶ ፡ ፍታወቅ ፡ ደመኢየሱስ ።

<u>በሕግ ፡ ሠርቲፊኬት ፡ በሰኔ ፡ ወር ፡ ፲፱፻፶፰ ፡ ዓ.ም. አግኝተው ፡ የሚመረቁ ፡ ተማሪዎች ።</u>

<u>(አሥመራ)</u> ።

አቶ ፡ ሀብተ ፡ ማርያም ፡ ደባስ ፡
አቶ ፡ ሐሚድ ፡ ሰማን ፡ ኢድሪስ ፡
አቶ ፡ ሑሴን ፡ ፋራሕ ፡
አቶ ፡ መሐመድ ፡ ሐንኪል ፡
አቶ ፡ መሐመድ ፡ ኑር ፡ ቁስማላ ፡
አቶ ፡ መሐመድ ፡ አሊ ፡
አቶ ፡ መሐመድ ፡ ኢብራሂም ፡ ሐንጋላይ ፡
አቶ ፡ መሐመድ ፡ ኢድሪስ ፡ ዑመር ፡
አቶ ፡ መኰንን ፡ አስረሱ ፡
አቶ ፡ መኰንን ፡ ደስታ ፡
አቶ ፡ መዋእል ፡ መብራሀቱ ፡
አቶ ፡ ሰሎሞን ፡ ካሕሳይ ፡
አቶ ፡ ሰይድ ፡ ከሊፋ ፡
አቶ ፡ ሳልሕ ፡ ሺፋ ፡
አቶ ፡ ሥዩም ፡ ይሕደጐ ፡
አቶ ፡ ሥዩም ፡ ፍስሐ ፡ ጽዮን ፡
አቶ ፡ በየነ ፡ አስፍሐ ፡
አቶ ፡ በየነ ፡ ገብረሥላሴ ፡
አቶ ፡ ብርሃነ ፡ ክፍለማርያም ፡
አቶ ፡ ተስፋት ፡ ዘሚካኤል ፡
አቶ ፡ ተስፋ ፡ ጽዮን ፡ ኢያሱ ፡
አቶ ፡ ተክኤ ፡ ገብረክርስቶስ ፡
አቶ ፡ ተኽለ ፡ ካሕሳይ ፡
አቶ ፡ አርአያ ፡ ገብረሥላሴ ፡
አቶ ፡ አፈወርቅ ፡ ጆርጅ ፡
አቶ ፡ ኢሳይያስ ፡ ሀብት ፡ ሥላሴ ፡
አቶ ፡ ከሊፋ ፡ መሐመድ ፡ ዓሊ ፡
አቶ ፡ ካሕሳይ ፡ አስፍሐ ፡
አቶ ፡ ካሣሁን ፡ ደረሰ ፡
የሻምበል ፡ ክብረ ፡ አብ ፡ በርሄ ፡
አቶ ፡ ክብሮም ፡ ዘይሉ ፡
አቶ ፡ ወልዱ ፡ በርሄ ፡
ያምላ ፡ አለቃ ፡ ወረታ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡
አቶ ፡ እቁባዝጊ ፡ አድከሞ ፡
ያምላ ፡ አለቃ ፡ ዮሐንስ ፡ ተክለየስ ፡
አቶ ፡ ገብረሚካኤል ፡ ብሥራት ፡
አቶ ፡ ገብረሥላሴ ፡ ገረንስኤ ፡
አቶ ፡ ገብረእግዚአብሔር ፡ ተስፋ ፡ ሚካኤል ፡
አቶ ፡ ገብረትንሣኤ ፡ ወልደሥላሴ ፡
አቶ ፡ ጸሐየ ፡ ዮሐንስ ፡
አቶ ፡ ጸጋዬ ፡ ባይሩ ።

<u>በሕግ ፡ ሰርቲፊኬት ፡ በሰኔ ፡ ወር ፡ ፲፱፻፶፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ አግኝተው ፡ የሚመረቁ ፡ ተማሪዎች ፡</u>

<u>(አሥመራ)</u> ።

አቶ ፡ ሐረገወይን ፡ ዘርአዮሐንስ ፡
አቶ ፡ መሐሪ ፡ ምስግና ፡
አቶ ፡ ሞሐመድ ፡ ኑር ፡ አህመድ ፡
አቶ ፡ ረዘነ ፡ ተስፋዬ ፡
አቶ ፡ ርእሶም ፡ ገብረማርያም ፡
አቶ ፡ ሳልሕ ፡ ካራር ፡
አቶ ፡ ስዩም ፡ ነጋሲ ፡
አቶ ፡ በርሄ ፡ ወልደሚካኤል ፡
አቶ ፡ በየነ ፡ ጊዮርጊስ ፡
አቶ ፡ ተስፋማርያም ፡ ነጋሽ ፡
አቶ ፡ ተስፋሚካኤል ፡ ገብረሚካኤል ፡
አቶ ፡ ተስፋሚካኤል ፡ ሐጐስ ፡
አቶ ፡ ተክሉ ፡ እተል ፡
አቶ ፡ ተክለሃይማኖት ፡ በርሄ ፡

አቶ ፡ ተወልደ ፡ መድኅን ፡ ገብረኪዳን ፡
አቶ ፡ ነጋሽ ፡ ደስታ ፡
አቶ ፡ አለም ፡ አማረ ፡
ግራዝማች ፡ አርአያ ፡ ሐጐስ ፡
አቶ ፡ አበበ ፡ ድባቸው ፡
አቶ ፡ አብርሃም ፡ ደስታ ፡
አቶ ፡ አብርሃም ፡ ገሀለእግዚእ ፡
አቶ ፡ አብዱሰላም ፡ ሙሳ ፡
አቶ ፡ አደም ፡ ሞሐመድ ፡ ሳለህ ፡
አቶ ፡ ዓምደብርሃን ፡ ገብረሥላሴ ፡
አቶ ፡ ዓምደማርያም ፡ ምስጉን ፡
አቶ ፡ ኢድሪስ ፡ ኢብራሂም ፡
አቶ ፡ ኤፍሬም ፡ ዑቁባገብርኤል ፡
አቶ ፡ ኪዳኔ ፡ ብርሃኔ ፡
አቶ ፡ ክብረአብ ፡ እዩብ ፡
አቶ ፡ ክፍለ ፡ ኪዳኔ ፡
አቶ ፡ ክፍለ ፡ ሃሐይ ፡
አቶ ፡ ዘሪሁን ፡ እየለ ፡
አቶ ፡ የማኔ ፡ ተክለ ፡
አቶ ፡ ይመስገን ፡ ሐይለ ፡ ጊዮርጊስ ፡
አቶ ፡ ዮሐንስ ፡ ኃይለ ፡
አቶ ፡ ደበሳይ ፡ ተስፋ ፡ ጋብር ፡
አቶ ፡ ትርጊያ ፡ ተስፋሥላሴ ፡
አቶ ፡ ጳውሎስ ፡ ኤጀል ።

<u>በሕገ ፡ መንግሥት ፡ በሰኔ ፡ ወር ፡ ፲፱፻፶፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ሰርቲፊኬት ፡ አግኝተው ፡</u>

<u>የተመረቁ ፡ ተማሪዎች ፡ (የእንግሊዝኛ ፡ ክፍል) ።</u>

የተከበሩ ፡ አቶ ፡ ሰይፈ ፡ ታደሰ ፡
የተከበሩ ፡ አቶ ፡ በየነ ፡ አብዲ ፡
የተከበሩ ፡ አቶ ፡ ታደሰ ፡ አያሌው ፡
የተከበሩ ፡ አቶ ፡ ኃይሉ ፡ ደምሴ ፡
የተከበሩ ፡ አቶ ፡ አለምነህ ፡ በላይ ፡
የተከበሩ ፡ ቄስ ፡ ኤርሚያስ ፡ ከበደ ፡
የተከበሩ ፡ አቶ ፡ ከበደ ፡ ኩሳ ፡
የተከበሩ ፡ አቶ ፡ ጥላሁን ፡ ኃይሌ ፡

<u>በሕገ ፡ መንግሥት ፡ በሰኔ ፡ ወር ፡ በ፲፱፻፶፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ሰርቲፊኬት ፡ አግኝተው ፡</u>

<u>የተመረቁ ፡ ተማሪዎች ፡ (የአማርኛ ፡ ክፍል) ።</u>

የተከበሩ፡ አቶ ፡ ለገሠ ፡ አበጋዝ ፡
የተከበሩ፡ አቶ፡መስፍን፡ኃይለ፡ማርያም፡
የተከበሩ፡ አቶ ፡ ሙሉዓለም ፡ ከልካይ ፡
የተከበሩ፡ አቶ ፡ ምገስ ፡ ወልደ ፡ ጻድቅ ፡
የተከበሩ፡ ወይዘሮ፡ራቢያ፡አብደልቃድር፡
የተከበሩ፡ አቶ፡ሰለሞን፡ሀብተ፡ጊዮርጊስ፡
የተከበሩ፡ አቶ፡ ሰይፈ፡ ያሬድ፡ ዓለማየሁ፡
የተከበሩ፡ አቶ ፡ ሽመልስ ፡ አበራ ፡
የተከበሩ፡ አስር ፡ አለቃ ፡ በረሄ ፡ ወልደ ፡
ገብርኤል ፡
የተከበሩ፡ አቶ ፡ በሪሁን ፡ ወንድምነህ ፡
የተከበሩ፡ አቶ፡ብስራት፡ወልደ፡መስቀል፡
የተከበሩ፡ አቶ ፡ ተሰማ ፡ ዲንሜ ፡
የተከበሩ፡ አቶ ፡ ተሾመ ፡ ባሀሩ ፡
የተከበሩ፡ አቶ ፡ ተክሌ ፡ ረዳ ፡
የተከበሩ፡ አቶ ፡ ተዘራ ፡ ሽበሺ ፡
የተከበሩ፡ አቶ ፡ ታየ ፡ ከበደ ፡
የተከበሩ፡ አቶ ፡ ታደሰ ፡ መድፉ ፡
የተከበሩ፡ አቶ ፡ ታፈሰ ፡ ሙላት ፡
የተከበሩ፡ አቶ ፡ ነምራ ፡ ዴሬሳ ፡
የተከበሩ፡ አቶ ፡ አበራ ፡ ባለህ ፡
የተከበሩ፡ አቶ፡አብድልቃድር፡ አህመድ፡
የተከበሩ፡ አቶ፡አብድልአዚዝ፡ሞሐመድ፡
የተከበሩ፡ አቶ ፡ አባተ ፡ አምበርብር ፡
የተከበሩ፡ አቶ ፡ አያሌው ፡ ጐቤ ፡
የተከበሩ፡ አቶ፡ አፈወርቅ፡ ወልደ፡ ኪሮስ፡
የተከበሩ፡ አቶ ፡ ኢብራሂም ፡ ሞሐመድ ፡
የተከበሩ፡ አቶ ፡ እንዳሻው ፡ በረደድ ፡
የተከበሩ፡ አቶ ፡ እንየው ፡ ገሠሠ ፡
የተከበሩ፡ አቶ ፡ ከበደ ፡ አጥናፍ ፡ ሰገድ ፡
የተከበሩ፡ አቶ ፡ ከበደ ፡ ቦረና ፡
የተከበሩ፡ አቶ ፡ ከበደ ፡ ሦሬ ፡
የተከበሩ፡ አቶ፡ ወልደ፡አማኑኤል፡ዱባለ፡
የተከበሩ አቶ ፡ ጌታነህ ፡ ከበደ ፡
የተከበሩ፡ አቶ ፡ ጋይም ፡ እስመላሽ ፡
የተከበሩ፡ አቶ ፡ ፍቅረሥላሴ ፡ ተስፋ ፡
የተከበሩ፡ ባላምባራስ፡ ፍቅሬ፡ ወልደየስ።